# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




**በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

**የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት (“የምድብ ‘ሐ’ሕንፃ”) በተመለከተ የተከናወነ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት**

**መጋቢት 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


ማውጫ ..... i

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ ..... I

(Executive Summery) ..... I

ክፍል አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አመሰራረት፡- ..... 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ..... 3

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት፡- ..... 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) ድርጅታዊ መዋቅር እና ሰው ኃይል ..... 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) የፋይናንስ ምንጭ ..... 7

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ..... 7

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ..... 8

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ..... 8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ..... 8

ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..... 8

የስራ ፍሰት መግለጫ (Process Description) ..... 10

ክፍል ሁለት ..... 11

ግኝቶች ..... 11

የሕንጻ ግንባታዎችና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ የሬጉላቶሪ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ተግባራዊ እንዲሆኑ ስለመደረጉ ..... 11

የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች ሲከናወኑ የህንጻ አዋጁ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ..... 11

የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ ..... 15

የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ያገኘ መሆኑ ..... 21

በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካልጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ ........ 23
በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን በተመለከተ ........ 29
በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን በተመለከተ.. 33
የሕንጻ ሹም ምደባን እና ውክልና በተመለከተ ........ 39
ሚ/ር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መከበራቸውንና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ 42
የአቅም ግንባታ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ ተገቢውን አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል እቅም እንዲፈጠር መድረጉን በተመለከተ ........ 45
የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ........ 51
ለማንኛውም የሕንጻ ምድብ ዓይነቶች የሚቀርቡ ዲዛኖች መዘጋጀት የተመዘገቡ ባለሞያዎች ስለመሆኑን ........ 52
በሕንጻ አዋጁ መሠረት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ መቋቋሙን በተመለከተ........ 55
በግንባታ ወቅት አስፈላጊው የደህንነት ጥንቃቄዎችን በማድረግ ግንባታዎች የሚከናወኑ መሆኑ በተመለከተ ........ 56
ሚ/ር መ/ቤቱ በሕንጻ ግንባታና መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፣........ 57
በሕንፃ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 58
ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን የተዘጋጀላቸው መሆኑን በተመለከተ ........ 58
ግንባታቸው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዘርፍ ወደ ሌላ ዘርፍ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ዲዛይን ብቁ መሆናቸውን መረጋገጡን በተመለከተ . 59
ከሕንጻ አዋጁ ጋር በተያያዘ ለሚ/ር መ/ቤቱ በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በተሰጡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ ........ 60
ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ ........ 63
ክፍል ሦስት ........ 67

መደምደምያ ........ 67

ክፍል አራት ........ 70

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 70

አባሪ 1 የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር ........ 74

አባሪ ሁለት፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 75

የኦዲት አካባቢ፡- የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን (“የምድብ ‘ሐ’ ሕንፃ”) በተመለከተ ........ 75

አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ ባላድርሻ አካላት ........ 78

አባሪ 4፡ በሕንጻ ግንባታ ወቅት የደረሱ ሞትና የአካል ጉዳት ........ 79

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive Summery)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ("የምድብ 'ሐ' ሕንፃን") ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የህንጻ አዋጆችና የህግ-ማዕቀፎች በከተሞችና በክልሎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል፣ ድጋፍና ዕገዛ መደረጉንና የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማጣራት ሲሆን በዚህ ዙርያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዳ የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ እንዲሁም ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህ የክዋኔ ኦዲት ተካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከ2008 እስከ 2010 የሶስት በጀት ዓመት እና የ2011 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ እነርሱም፡-

- የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎች በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይናቸው እንዲጸድቅ የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም የመንግስት ፕሮጀክቶች ተገቢው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌላቸው መሆኑ እና የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው፣ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግላቸው እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣
- በከተሞች ውስጥ የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው የማይገነቡ መሆኑ (ኤሌክትሮ ሜካኒካል ፕላንና ትንታኔ ፣ የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣ አርክቴክቸራል፣ ኤሌክትሪካል፣ እና ሳኒቴሪ ፕላን ትንታኔ ሪፖርት ሳይይቀርብ ወዘተ…የግንባታ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ)
- በከተሞች የሚሰጠው የፕላን ስምምነት በከተሞቹ መሪ ፕላን ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት እየተረጋገጠ አለመሆኑ፣

- በከተሞች የሚዘጋጁ የዲዛይን (ፕላኖች) እና የሚገነቡ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን የሚመቹ ወይም ፍትሀዊ ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳትፎአቸውን ያካተቱ መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ የማይከታተል መሆኑ፣
- በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሂደትን ተከትለው የማይገነቡ በመሆኑ ህገወጥ ግንባታዎች (ሴት ባክ (የተፈቀደላቸው ወሰን) ሳይጠብቁ መገንባት፣ ከተፈቀደው ከዲዛን ውጪ ወለል መጨመር እና የግንባታ ፈቃድ ሳይኖር ግንባታ መገንባት) መስፋፋታቸው ፣
- በከተሞች በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ (ለአገልግሎት ብቁ ሲሆኑ) እና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣ እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸውም ቢሆን ሂደቱን ተከትሎ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መከበራቸውንና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው የተደረገው ክትትልና ድጋፍ በዕቅዱ መሰረት ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- በህንጻ አዋጁ መሠረት በሕንጻ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በከተሞች ያልተቋቋመ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በመሆኑም ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦችን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

- የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች እንደሌሎቹ የሕብረተሰቡ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ ለማስቻል በሕንጻ አዋጁ መሰረት የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ፣ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው እንዲሁም ሕንጻው ለአገልግሎት ብቁ መሆኑ እየተረጋገጠ የመጠቀሚያ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ቢደረግ፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ሕግን ተከትለው በተሟላ መንገድ እየተፈጸሙ መሆኑን ሚኒስተር መ/ቤቱ የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና የግንባታ ፈቃድ ሳይወስዱ ግንባታ የሚጀምሩ ተጠያቂ መሆናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች የከተማውን መሪ ፕላን መሰረት በማድረግ የፕላን ስምምነት አግኝተው መገንባታቸውን ሚኒስተር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡
- ተዘጋጅተው የቀረቡ የዲዛይን ጥናቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስገዳጅ የዲዛይን ስታንዳርድ በመተግበር ተደራሽ ዲዛይን (Accessible Design) እንዲሁም ሁሉን አቀፍ ዲዛይን (Universal Design) በማጣመር ተግባራዊ እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን ከተሞች እያረጋገጡ ስለመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሂደቱን ተከትለው በሕጉ መሰረትና በተሟላ መንገድ እንዲተገበር እየተደረገ ስለመሆኑ ሚኒስተር መ/ቤቱ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና የተጠያቂነት ሥርዓት ስለመኖሩ ሊከታተል ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ተከትለው በሕጉ መሰረትና በተሟላ መንገድ እንዲተገበር መድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ያለመጠቀሚያ ፈቃድ በከፊል አገልግሎት ለሚሰጡና ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው አገልግሎት ለሚሰጡ ሕንጻዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ያሉ የሕንጻ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም ወደፊት የሚወጡ ሕጎች ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በግንባታ ፈቃድ፣ በግንባታ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን (ቅሬታዎች) ለመፍታት በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በሌላቸው ከተሞች ቦርድ እንዲቋቋም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተለያዩ ሀብቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደሆኑ የፊዚካልና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማቶች እና የግንባታ ውጤቶችን የሚለውጥ እና እሴት የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ወሳኝ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የኢኮኖሚና የማህበራዊ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሁም ፋብሪካዎችና መኖርያ ቤቶች ከተያያዥ ልማቶች ጋር የሚጠኑበት፣ የሚታቀዱበት፣ የሚቀረጹበት፣ የሚጠገኑበት፣ ነባር ግንባታዎች ተስተካክለው ሌላ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚቀየሩበትና አገልግሎት ላይ የሚውሉበትን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡

2. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማዊ ገፅታ መላበስ የጀመረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በፕሮጀክት ደረጃ እንደነበር ታሪክ ያወሳል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ የግንባታ ቅርሶች የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ጥበብ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን የሚያሳዩ ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ ይህም በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለዜጎች ማቅረብ የሚገባውን መሰረተ ልማት አቅርቦትና ጥራት በማሳደግ ሂደት መሪ ተዋናይ በመሆን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ምቹ ሁኔታ ያበረከተ ቢሆንም ከዘርፉ የሚጠበቀውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት በአጥጋቢ ሁኔታ ጥቅም ሳያስገኝ ቆይቷል፡፡

3. ለዚህ አነስተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱት መንስኤዎች ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራባቸው አግባብነት ያላቸው ስትራቴጂዎች፣ አዋጅ፣ የህግ ማዕቀፎች በአግባቡ ያለመሟላትና አለመተግበራቸው፣ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ አለመሻሻላቸው፣ የሰለጠነና የሙያ ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ የሥራ አመራር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር የተሳለጠ አለመሆን፣ ባለሞያዎች በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ ለዘርፉ የተፋጠነ ዕድገት በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ አለመፍጠር፣ የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ያለመጠናቀቃቸው፣ የባለሞያዎች፣ ተቋራጮችና የአማካሪዎች አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ጎልቶ መታየት እና የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥሩ የተጠናከረ (አጥጋቢ) አለመሆኑ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

4. በመሆኑም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እየደረሰ ያለው የምህንድስና ግንባታ እና ዲዛይን እቅዶች ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም ባለመገንባቱ ምክንያት የኮንስትራክሽን ግንባታዎች በወጣላቸው መርሀ-ግብር፣ ወጪና ጥራት ደረጃ አለመገንባት፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ ሕንጻዎች ደረጃቸውን ጠብቀው አለመገንባት፤ እየተገነቡ ያሉ ሕንጻዎች ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለሴቶች ተስማሚ፣ ምቹና ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ የተገለፁትን ችግሮች ለመፍታትና በዘላቂነት የኮንስትራክሽን ግንባታዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ አስተዋፅኦ በአግባቡ ለመጠቀም እና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ብሎም የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን ኢንዲስትሪ የዘርፉን አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት አሁን ካለበት 8.5 በመቶ ከፍ ለማድረግ እንዲቻል መንግስት ትኩረት በመስጠት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አመሰራረት፡-

5. በ1960ዎቹ ድረስ የአገር ውስጥ ስራ ተቋራጮችና አማካዎች ጥቂት ነበሩ፤ በመሆኑ ትላልቅ የህንጻና የመንገድ ግንባታዎች በዓለም አቀፍ አማካሪዎች ይከናወኑ የነበረ ሲሆን፤ ባለሙያዎቹም ከውጭ ይመጡ ነበር፡፡ በመቀጠል በደርግ ሥርዓት ተጠሪነቱ ለቤቶች፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል የኢትዮጵያ ህንፃ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር191/1972 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በመቀጠል በ1974 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 216/1974 በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ “የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር” ተብሎ ተቋቋመ፡፡ ሆኖም ግን በዛን ጊዜ የነበረው ሥርዓት የግል ድርጅቶችን ስለማያበረታታ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፉ በሚፈለገው መጠን ሊያድግ አልቻለም፡፡

6. መንግስትም ይህን በመረዳት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ በመፍጠር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንደገና አቅም እንዲኖረው በማድረግና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተለያዩ ሀብቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደሆኑ የግንባታ ውጤቶች የሚለውጥ እና እሴት የሚፈጥር የኢኮኖሚያዊ ልማት ዘርፍ ሲሆን ኢንዲስትሪው የአንድን ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሁም በዘላቂነት ለማሻሻል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በሚል ተቋቁሞ

የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፤ እንደገና የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ 691/2003 እንዲቋቋም በማድረግ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል ተቋቁሞ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

7. በመቀጠልም መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት በ2017 ሀገራዊው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የማስፈጸም አቅም ለማሳደግ እና የአገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን አሟልቶ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን ለማስቀጠልና ልማቱን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስኬድ የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን ባወጣው አዋጅ 916/2008 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ እንዲወጣ በማድረግ የኮንስትራክሽን ዘፍር ስራዎችን ሲሰራ ቆየ፡፡ መንግስት እንደገና የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቃቀር አስፈላጊ በመሆኑ፣ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለዉን ለዉጥ ውጤታማ፣ ዘላቂ እና ተቋማዊ ለማድረግና የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም በድጋሚ ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጋር መልሶ እንዲዋሃድ በማድረግ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) ራዕይ፣ ተልዕኮ፣

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ)

8. በ2017 አገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የማስፈጸም አቅም አድጎ እና የአገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን አሟልቶ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት ነው፡፡

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኮንስትራክሽን ዘርፉ) ተልዕኮ

9. የዘርፉን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀና ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት፡-

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡-

- የከተማ ልማትንና ኮንስትራክሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ፓኬጆችን እና ፕሮግራሞችን ይቅርጻል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትናአገራዊ ስፓሻል ፕላን እንዲሰራ በማድረግ የተቀናጀ የአከታተምሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ከተሞች ከአገር አቀፍና ከክልል አቀፍ የልማት ዕቅዶችና ከተቀናጀ የከተሞች ፕላን ጋር ተጣጥመው የሚመሩበትን አቅጣጫ ይነድፋል፤
- ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናቶችን ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤ ከተሞች የአካባቢያቸውን የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የተመጣጠነ የከተሞች ዕድገትና የህዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤
- የከተሞችን መሬት በቁጠባ መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ስልት ይነድፋል ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
- የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ለክልሎች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፤ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤
- የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፤ የከተማ የምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

- የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፤
- የነፃ ገበያ ሥርዓት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የካዳስተር እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይት ሥርዓት እንዲገነባ ያደርጋል፤ በከተሞች ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የለማ መሬት አቅርቦት ለማረጋገጥ ድጋፍ ይሠጣል፤
- የከተሞች ልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ያጠናል፣ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ፈንድ ያሰባስባል፣ ለአፈጻጸሙም ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
- ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲጸድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤
- የኮንስትራክሽን ዘርፉን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ ለዘርፉ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ይተገብራል፤
- በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- በማንኛውም ዘርፍ የሚደረጉ የኮንስትራክሽ ሥራዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ደረጃ ያወጣል፣ መከበራቸውን ይከታተላል፤
- በፌደራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
- የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በከተሞች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ሃይል አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤
- አገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ብቃትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

- በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰማሩ መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፤ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

11. **በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕንጻ አዋጅ 624/2001 በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-**
   - በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራባቸው ልዩ ልዩ ኮዶችን ያዘጋጃል፤
   - ለየሕንጻ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ያዘጋጃል፤
   - አዋጁ በክልሎችና በከተሞች ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፤
   - ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፌደራል መንግስቱ አካላት ጋር በመቀናጀት ክልሎችና ከተሞች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) ድርጅታዊ መዋቅር እና ሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ **(ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)**

### የሰው ኃይል

13. የሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኮንስትራክሽን ዘርፉ) 468 ሠራተኞች በመዋቅር የተፈቀደለት ሲሆን እስከ ታህሣሥ 30 2011 ዓ.ም 244 (52.14%) ሰራተኞች ነበሩት፡፡ ይህም በት/ት ደረጃ ሲገለፅ ሁለተኛ ዲግሪ ወንድ 42 ሴት 12 በድምሩ 54(22.13%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ወንድ 80 ሴት 49 በድምሩ 129(52.90%)፣ ዲፕሎማ ወንድ 10 ሴት 5 በድምሩ 15(6.15%)፣ ሰርተፍኬት ወንድ 2 ሴት 3 በድምሩ 5(8.61%)፣ ቲቪቲ ወንድ 15 ሴት 6 በድምሩ 21(2.05%) እንዲሁም የተቀሩት 12ኛ ክፍልና ከዚያ በታች ወንድ 9 ሴት 11 በድምሩ 20(8.20%) የት/ት ደረጃ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ (የኮንስትራክሽን ዘርፉ) የፋይናንስ ምንጭ

14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጣለበትን የሥራ ድርሻ እና በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገውን በጀት ከፌዴራል መንግስት በሚመደብለት በጀት የሚያገኝ ሲሆን ከ2008 እና 2010 በጀት ዓመት 2011 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የተመደበለት የመደበኛ ካፒታል በጀት ገቢና ወጪው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**የገቢና ወጪ መግለጫ**

| በጀት ዓመት | የተመደበ በጀት | | | ሥራ ላይ የዋለ በጀት | | | ሥራ ላይ የዋለው (በ %) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከመደበኛ በጀት | ከካፒታል በጀት | ጠቅላላ የተመደበ በጀት | ከመደበኛ በጀት | ካፒታል | ጠቅላላ ሥራ ላይ የዋለ | |
| **2008** | 46,432,823.74 | ---------- | 46,432,823.74 | 31,186,181.29 | ------ | 31,186,181.29 | 67% |
| 2009 | 96,085,371.00 | ----------- | 96,085,371.00 | 75,121,932.77 | ------ | 75,121,932.77 | 78% |
| 2010 | 115,065,252.00 | 15,000,000 | 130,065,252.00 | 91,919,886.34 | ------ | 91,919,886.34 | 71% |
| 2011 | 121,870,500.00 | - | 121,870,500.00 | 37,330,999.35 | - | 37,330,999.35 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ | 31% |
| **ጠቅላላ ድምር** | **379,453,946.74** | **15,000,000** | **394,453,946.74** | **235,558,999.75** | **------** | **235,558,999.75** | **60%** |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

15. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ (**"የምድብ 'ሐ' ሕንፃን"**) ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል የህንጻ አዋጆችና የህግማዕቀፎች በከተሞችና በክልሎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል፣ ድጋፍና ዕገዛ መደረጉንና የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማጣራት ሲሆን በዚሁ ዙርያ የተደረገ ማጣራት ሲሆን በዚህ ዙርያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዳ የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "**የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ** A (**"የምድብ 'ሐ' ሕንፃን") ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ**" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

17. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) **ተዘጋጅተዋል**፡፡ እነርሱም፡-

   I. የሕንጻ ግንባታዎችና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ የሬጉላቶሪ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማረጋገጥ፣

   II. በሕንፃ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን ማጣራት

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

18. ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) **ለመመዘን** የሚረዱ 28 **የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች** (Evaluative Criteria) **ተዘጋጅቷል**፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የሚ/ር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የሕንጻ አዋጅ፣ የሕንጻ ደንብ፣ የሕንጻ መመሪያ፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣ የሚ/ር መ/ቤቱ እቅድና የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች በሚኒስቴር መ/ቤ (በቀድሞው ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር) አስተያት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ **የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 1 ተያይዟል**፡፡

## ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከ2008 እስከ 2010 የሶስት በጀት ዓመት እና የ2011 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ያለውን አፈጻጸም

ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ በተመረጡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡

20. ዝርዝር የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኮንስትራክሽን ዘርፍ) ሲሆን በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች፣ በሶስት ክልሎች እና በነዚህ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ በናሙና በተመረጡ ከተሞች ሥር በሚገኙ የሕንጻ ሹም ጽ/ቤቶች፣ የኮንስትራክሽን ቢሮ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመጠየቅና በመከለስ ነው፡፡ በናሙና በታዩት ከተሞች የግንባታ ፈቃድ ሳይኖራቸው የተገነቡ፣ በክትትልና ቁጥጥር ሂደት ያላለፉና አገልግሎት ላይ የዋሉና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖራቸው አገልግሎት የሚሰጡ፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች ተደራሽ ያልሆኑ ህንጻዎች እንዲሁም በህገወጥ መንገድ የተገነቡ ሕንጻዎችን በአካል በቦታው ተገኝቶ በማየትና ፎቶ በማንሳት የኦዲት ሥራው ተከናውኗል፡፡ በናሙና ተመርጠው የታዩ የከተማ አስተዳደሮች፣ ክልሎች፣ ከተሞች፣ የሕንጻ ሹም ጽ/ቤቶች፣ የኮንስትራክሽን ቢሮዎች እንዲሁም ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ዝርዝር **በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡**

## የስራ ፍሰት መግለጫ (Process Description)

## የኮንስትራክሽን ደረጃዎች፣ ህጎች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት

21. የኮንስትራክሽን ሥራዎችና አገልግሎቶችን መለየት፣ ደረጃዎች አወጣጥና አተገባበር የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

- የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ የሚተገበሩበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋ፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
- የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች እና የኢንዱስትሪው የስነ-ምግባር መርሆች መፈጸማቸው የሚረጋገጥበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
- የግንባታ ፈቃድ፣ ቁጥጥር እና የመጠቀምያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲተገበር ያደርጋል፡፡
- የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶች ስታንዳርዶች እና የኢንዱስትሪው የስነ-ምግባር መርሆዎች አፈጻጸም ለክልሎችና ከበለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየት የጋር መድረክ ያዘጋጃል፡፡
- የግንባታ ውጤቶች የዲዛይን እድሜያቸውን ባገናዘበ ሁኔታ እድሳትና ጥገና የሚደረግበትን እና እንደአስፈላጊነቱ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
- ቀደም ሲል የተገነቡ ሆነው በስራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ክትትል ይደረጋል፡፡
- ግንባታዎች ከታለመላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ሲፈለግ፣ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ክትትል ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### የሕንጻ ግንባታዎችና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ የሬጉላቶሪ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ተግባራዊ እንዲሆኑ ስለመደረጉ

### የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች ሲከናወኑ የህንጻ አዋጁ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

22. የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች በህንጻ አዋጅ፣ ደንብና መመርያው መሰረት እንደማንኛውም ሕንጻ ግንባታ የፕላን ስምምነት ሊያገኝ፣ የግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትሎ ሊገነባ ይገባል፡፡ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሂደትን ተከትሎ መስፈርቱን ማሟላታቸው ተረጋግጦ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተቋማቱ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግላቸው እና ግንባታቸው ሲጠናቀቅ የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሂደትን ተከትሎ ስለመሰራታቸው ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

23. ይሁን እንጂ

- የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎች ሙሉ ለሙሉ (ባጠቃላይ) በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይናቸው እንዲጸድቅ የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም የመንግስት ፕሮጀክቶች ተገቢው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌላቸው መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ ለአማራ ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በጅማ፣ በነቀምትና በመቱ ከተሞች በሸኔ፣ በቆቦ፣ መርሳ፣ አላማጣ፣ መቀሌ፣ በወልድያ በሻሸመኔ፣ በሆሳዕና፣ በአፋር፣ ሀረር ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ ቤጋምቤላ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል፣ የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች እንደማንኛውም ግንባታ በህንጻ አዋጁ መሰረት የፕላን ስምምነት ሳያገኙ ግንባታ የሚካሄድ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው፣ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግላቸው እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣

- የመንግስት ግንባታ በአራዳ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ 4 ኪሎ አካባቢ (እሪ በከንቱ አካባቢ) የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው በግንባታ ወቅት የአካል ጉዳት የደረሰ መሆኑ ታውቋል፡፡





*በአዲስ አበባ የፌዴራል መንግስት ግንባታ ተነዶ በ12 ሰዎችላይ ጉዳት ያደረሰ ህንጻ*

- በናሙና በታዩ ክልሎችና ከተሞች የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎች የፕላን ስምምነት ሳያገኙ ግንባታ የሚካሄድ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው፣ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግላቸው እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ10 ሩም ክፍለ ከተሞች የተገነቡ የመንግስት ግንባታዎች እና የጋራ መኖርያ ቤቶች (ኮንዶሚኒየም) የግንባታ ፈቃድ ሂደትን ተከትለው፣ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖራቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመንግሰት ኮንስትራክሽን የሚሰሩ ዲዛይኖች ጥራት በአግባቡ ባለመዘጋጀታቸው ለቫሬሽን በር መክፈቱ፣
- በቤንሻንጉል ጉምዝ የክልሉና እና አሶሳ ከተማ የመንግስት ግንባታዎች በህንጻ አዋጁ፣ በደንብና መመርያ መሰረት ዲዛይናቸው አለመፅደቁ፣
- በቤንሻንጉል ጉሙዝ የመንግስት ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ ወስደው እንዲገነቡ የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮም ሆነ በህንጻ ሹም ጽ/ቤት ጥረት የማይደረግ መሆኑ፣

- በትግራይ ክልል ቢሮ የሚሰሩ 121 ሕንጻዎች የሕንጻ አዋጁን አሟልተው አለመገንባታቸው በጥር 2010 ዓ.ም በትግራይ፣ በአፋርና በአማራ ክልል የተደረገ ክትትልና ድጋፍ ላይ ተገለጸ መሆኑ፣
- በአፋር ክልል፣ በሀረር ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል እና በትግራይ ክልሎች የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎች ምንም አይነት ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአፋር ክልል የመንግስት ተቋማት ዲዛይንና የሥራ ዝርዝራቸውን ለህንጻ ሹም አቅርበው ዲዛይናቸው ተመርምሮና የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ግንባታ እየገቡ አለመሆኑ፣ እንዲሁም የመንግስት ፕሮጀክቶች የናሙና ፍተሻ ሳይደረግላቸው ወደ ግንባታ የሚገቡ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን 17 ህንጻዎች፣ በደቡብ ጎንደር ዞን 9 ሕንጻዎች፣ በሰሜን ወሎ ዞን 8 ሕንጻዎች፣ በዕራብ ጎጃም ዞን 3 ሕንጻዎች፣ በኦሮሚያ ዞን 3 ሕንጻዎች፣ በመሐል ጎንደር 17 ሕንጻዎች፣ በደቡብ ወሎ 1 ሕንጻ፣ በአዊ ዞን 59 ሕንጻዎች፣ ዩኒቨርስቲ ሕንጻዎች በሙሉ እና በክልሉ የሚገኙ አንጎት፣ ጋሻና ጋዞ ወረዳዎች የሚሰሩ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የግንባታ ፈቃድ ሳይኖራቸው የተገነቡ መሆናቸው፣
- በአማራ ክልል በፌደራል እና በክልል መንግስት በጀት የህንጻ አዋጁን ሰያከብሩ በከተማው ውስጥ የሚገነቡ ግንባታዎች ላይ አዋጁን ተከትሎ እርምጃ አለመወሰዱ አዋጁን ያላከበሩ የፌደራልና የክልል መንግሰት ፕሮጀክቶች ወደ ስራ የሚገቡት ላይ እርምጃ ያለመወሰዱ፣ (የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ስቴድየም፣ የጤናና የትምህርት ተቋማቶች፣ ቤዛዊት የቤተ መንግሰት ግንባታዎች እና የመንግስት ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ፕላን ሳያጸድቁና የግንባታ ፈቃድ ሳይወስዱ ባጠቃላይ የህንጻ አዋጁን ሳያከብሩ በክልሉ እየተገነቡ መሆኑ፣
- በጋምቤላ ክልል የመንግስት ፕሮጀክቶች ሙሉ በሙሉ የግንባታ ፈቃድ፣ አስፈላጊው የህንጻ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ በህንጻ አዋጁና ደንቡ መሰረት በህንጻ ሹም ስር እንዲያልፍ አለመደረጉ፣
- በሶማሌ ክልል በጅጅጋ ከተማ በመንግስት በጀት የሚገነቡ ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ እያወጡ ወደ ስራ እንዲገቡ አለመደረጉ

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት እና ለኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. ስለጉዳዩ የክልሎች የኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎች፣ የከተሞች የሕንጻ ሹም ኃላፊዎች ተጠይቀው የመንግስት ሕንጻ ግንባታን በተመለከተ የመንግስት ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ የማይወስዱ፣ በክትትልና ቁጥጥር ስር የማያልፉና ሕንጻው ሲጠናቀቅ (ለአገልግሎት ብቁ ሲሆን) የመጠቀሚያ ፈቃድ የማይወስዱ መሆናቸው በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

25. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ሲመልሱ

- አዎ ትክክል ነው የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች ችግር እንዳለበት እንደሚያውቁ፣
- ለክልሎችና ለከተሞች በህንጻ አዋጁ መሰረት እንዲሰሩ ደብዳቤ የጻፉ መሆናቸው፣
- ነገር ግን የመንግሰት ግንባታዎች የሕንጻ አዋጁን ሳያከብሩ እንደሚሰሩና በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታዎችና ሌሎች ግንባታዎችም በሕንጻ ሹም የማያልፉ መሆናቸውን በቀረበላቸው ቃለመ-ጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

26. ስለጉዳዩ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት አስተያየት የመንግስት ሚ/ር መ/ቤቱ አንዱ ከድጋፍና ክትትል ስራው በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሰራቸው ተግባራት በመሆኑ ከሦስት ዓመት በፊት የነበረው የመንግስት ግንባታዎች በህንጻ አዋጁ እንዲልፉ ከማድረግ ጋር በተገናኘ ሰፊ ክፍተቶች ያሉ ቢሆኑም፤ ባለፈው ጊዜ ሚ/ር መ/ቤቱ በ2010 ዓ.ም እና በ2011 ዓ.ም በተደረገው የድጋፍና የክትትል ሥራ በኦሮሚያ፣ ትግራይ አማራ፣ ደቡብ፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ በቂ ነው ባይባልም የመንግስት ግንባታዎች በህንጻ አዋጁ እንዲያልፍ ለማድረግ ጥረት መደረጉን፣ ወደ ሥራ ያልገቡትም ክልሎች ላይ ከዚህ ችግር መውጣት በሚችሉበት መልኩ የችግሩ አሳሳቢነት በመግለፅ ግብረ-መልስ እንዲደርሳቸው ተደርጓል በማለት ገልፀዋል፡፡

27. የሚኒስቴሩ ስራ ኃላፊዎች በቃለ- መጠይቅ ወቅት፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና በመውጫ ስብሰባ ላይ ይህን ይበሉ እንጂ የሰጡት ሃሳብ ተመሳሳይ አለመሆኑና ድጋፍና ክትትል አድርጎ ግብረመልስ ከመስጠት ውጪ ሌሎች እርምጃዎች ለመውሰድ ያደረገው ጥረት ባለመኖሩና በመንግስት ግንባታዎች ላይ ያለው ክፍተት በየአመቱ ተመሳሳይ በመሆኑ እንዲሁም የመንግስት ግንባታዎችን በተመለከተ

የተደረገው ድጋፍና ክትትል ግብረ-መልስ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድስ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች በሕንጻ አዋጁ፣ ደንብና መመርያ መሰረት የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ፣ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው እና ሕንጻው ለአገልግሎት ብቁ ሲሆን የመጠቀሚያ ፈቃድ በመውሰድ ወደ አገልግሎት እንዲገቡ የማይደረግ ከሆነ የሕብረተሰቡ ደህንነትና ጤንነት እንዳይጠበቅ፣ ሕንጻው አስጊ እንዲሆን እና የኢንደስትሪውን ሥነ-ምግባር ጠብቀው እንዳይከናወኑ እና የጥራት ደረጃቸውን ጠብቆ እንዳይገነባ በር ይከፍታል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ያወጣውን የህንጻ አዋጅና የወጡ የህግ ማዕቀፎች ራሱ በተሟላ መንገድ በአግባቡ የማይተገበር ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፍት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ

29. በከተሞች ውስጥ የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው ሊገነቡ ይገባል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት ግንባታዎች መሰራታቸውን በዓመታዊ እቅድ በመያዝ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎችና (በአማራ፣ ኦሮሚያና በደቡብ)ና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የሚገነቡ የመንግስት ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ ሂደትን ተከትለው ያልተገነቡ መሆኑ፣

- ❖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡-
    - ➢ በ10ሩም ክፍለ ከተሞች የተገነቡ የመንግስት ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ ሂደትን ተከትለው (የፕላን ስምምነት፣ ዲዛይናቸው በሕንጻ ሹም ሳይጸድቅ (ሳይገመገም) እና የግንባታ ፈቃድ ሳይሰጣቸው መገንባታቸው፣
    - ➢ በ2009 ዓ.ምና በ2010 ዓ.ም ከተሰጡ 36 የግንባታ ፈቃድ የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ (ቅፅ 001) በፈቃድ ጠያቂዎቹ ሞልተው ሲያመጡ ፈቃድ ሰጪው መሞላቱን የማያረጋግጥ መሆኑ
    - ➢ በ2009 ዓ.ምና በ2010 ዓ.ም ከተሰጡ 36 የግንባታ ፈቃድ የፕላን ስምምነት ባልተወከለ ክፍለ ከተማ ባለ የስራ ሂደት የተሰጠ መሆኑ፣ የግንባታ ፈቃዱን የሚያጸድቀው ሕንጻ ሹሙ ሳይሆን ውክልና ባልተሰጠው የስራ ሂደት መሆኑ፣

እንዲሁም የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ (ቅፅ 003) በፈቃድ ጠያቂዎቹ ሞልተው ሲያመጡ ፈቃድ ሰጪው መሞላቱን የማያረጋግጥ መሆኑ፣

- የጸደቁ የኤሌክትሪካል ዲዛይን ሪፖርቶች የሚገልጹት ዲዛይኑን ሳይሆን የዲዛይን አሰራር ሂደት መሆኑ እና የኤሌክትሪካል ሪፖርቶች ለተለያዩ የህንጻ ፕሮጀክቶች ተመሳሳይ ኮፒ መሆናቸው፣
- የጸደቁ የህንጻ ዲዛኖች የሳኒቴሪ ዲዛይን ሪፖርቶች የሚገልጹት ዲዛይኑን ሳይሆን የዲዛይን አሰራር ሂደት መሆኑ እና የሳኒተሪ ዲዛይን ሪፖርቶች ለተለያዩ የህንጻ ፕሮጀክቶች ተመሳሳይ ኮፒ መሆናቸው፣
- ባብዛኛው የአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት የጸደቁ ዲዛይኖች ደህንነቱ የተረጋገጠ አለመሆኑ፣
- በአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት የሚጸድቁ የሕንጻ ዲዛይኖች አንድ አርክቴክቸራል ዲዛይን (የሥነ ህንጻ ንድፍ) ሲጸድቅ ማካተት ያለበት የመዳረሻ መንገድ ስያሜ፣ ወደ ህንጻው መግቢያ አመላካች ምልክት፣ የተፈጥሮ የመሬት ተዳፋት ፕላን (Contour Plan)፣ ከዋናው ፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ጋር የሚገናኝ ከሆነ የማስወገጃ መስመር ያለበት ቦታ ርቀት፣ የጣርያ የተፋሰስ አቅጣጫ የተዳፋትነት መጠን እና የመሳሰሉት ያካተቱ አለመሆኑ፣
- በአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት የሚጸድቁ የሕንጻ ዲዛይኖች ግንባታው የሚሰራበትን አካባቢ የማያሳዩ፣ በእስኬል ያልተሰሩ እና በግልጽ የማይታዩ በቂ መረጃ መስጠት የማይችሉ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት የሚጸድቁ የሕንጻ ዲዛይን ሪፖርት ፍዚታዊ ስሌት (Statical Calculaion) የግንባታውን ዲዛይን አጠቃላይ መነሻ (Fundamental requirement) እና ታሳቢዎቹን (Action to be Considered) የሚዘረዝር መግቢያ የሌለው እና ለዲዛይን የተጠቀሙበትን ኮድና ስታንዳርድ ያልተጠቀሰ መሆኑ በቀን29/08/2010 ዓ.ም ዲዛይን የጸደቀላቸው የሕንጻ ፕሮጀክቶች የዲዛይንና ተያያዥ ሰነዶች አጸዳደቅ ሂደት በተመለከተ

በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገ የኮንስትራክሽን ኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

31. እንዲሁም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በቡታጅራና በሀዋሳ ከተሞች እንደዚሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፍኖተ ሰላምና በባህርዳር ከተሞች በናሙና ካየናቸው የተሰጡ ግንባታ ፈቃድ፡-

- ኤሌክትሮ ሜካኒካል ፕላንና ትንታኔ የማይቀርብ መሆኑና አልፎ አልፎ የቀረበውም ቢሆንም ዝምብሎ ሳይጸድቅ እንዲያልፍ የሚደረግ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ ከተማ ከተሰጡ 7 የግንባታ ፈቃድ ውስጥ 7ቱም የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣ አርክቴክቸራል፣ ኤሌክትሪካል፣ እና ሳኒቴሪ ፕላን ትንታኔ ሪፖርት ሳይይኖረው የግንባታ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ፣
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአፈር መመርመሪያ ድርጅት የሌለ መሆኑ፣ እንደዚሁም የአፈር ምርመራ ሪፖርቱ የሚያሳየው (Standard penetration test) መሆኑ፣
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከተሰጡ 11 የግንባታ ፈቃድ ውስጥ 11ዱም ኤሌክትሪካል፣ ሳኒተሪ፣ የእሳት አደጋ ፕላን ሪፖርት እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት እንዲሁም ስትራክቸራል ሪፖርት ህጋዊ ማህተም ሳይኖራቸው የግንባታ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዳማ ከተማ ከተሰጡ 7 የግንባታ ፈቃድ ውስጥ 7ቱም ኤሌክትሪካል፣ ሳኒተሪ፣ የእሳት አደጋ ፕላን ሪፖርት እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት ሳያቀርቡ የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ከ7ቱ ውስጥ ሁለቱ ብቻ የአፈር ምርመራ ሪፖርተ ያላቸው መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በቢሾፍቱ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ ናሙና በመምረጥ ያየናቸው 9 ባለሃብቶች ኤሌክትሪካል፣ ሳኒተሪ፣ የእሳት አደጋ ፕላን ሪፖርት እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት ሳያቀርቡ የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ከ9ኙ ውስጥ 3ቱ የአፈር ምርመራ ሪፖርተ የሌላቸው መሆኑ፣

- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ ናሙና በመምረጥ ያየናቸው 2 ባለሃብቶች ስትራክቸራል፣ ሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪካል ሪፖርት ህጋዊ ማህተም ሳይኖር የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በቡታጅራ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ በናሙና ከታዩት 6 ባለሀብቶች ውስጥ 6ቱም ኤሌክትሪካልና ሳኒተሪ ሪፖረት የሌላቸው መሆኑ እና ከ6 ውስጥ 2 ባለሀብቶች ስትራክቸራል ሪፖርት ህጋዊ ማህተም ሳይኖራቸው የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህብቦች ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ በናሙና ከታዩት 6 ባለሀብቶች ኤሌክትሪካልና ሳኒተሪ ሪፖርት የሌላቸው መሆኑ እና ከስድስቱ ውስጥ 1ባለሀብት ብቻ ስትራክቸራል ሪፖርት ህጋዊ ማህተም ሳይኖረው የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፍኖተ ሰላም ከተማ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ በናሙና ከታዩት 15 ባለሀብቶች የአሌክትሪካል ሪፖርትና ሳኒተሪ ሪፖርት የሌላቸው መሆኑ፣ ከ 15 ውስጥ 4 የአፈር ምርመራ ሪፖርት የሌላቸው መሆኑ፣ ከ15 ውስጥ 2 በላሀብቶች ስትራክቸራል ሪፖርት ህጋዊ ማህተም የሌላቸው መሆኑ፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፍኖተ ሰላም ከተማ የግንባታ ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ በናሙና ከታዩት 10 ባለሀብቶች የአሌክትሪካል ሪፖርትና ሳኒተሪ ሪፖርት ሳቀርቡ የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- ዲዛይን በሚጸድቅበት ጊዜ ከተዳፋት (Ramp) በስተቀር ለአካል ጉዳተኞች በየወለሉ የሚመቹ ሆነው መጸዳጃ ቤቶችና የመኪና ማቆሚያዎች ስለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- የባለመስታወት ግድግዳ ለሚገጠምላቸው ሕንጻዎች ነጸብራቁ በነዋሪው ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑ በቅድምያ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- የመድህን ዋስትና የማይቀርብ መሆኑ፣

- የአሳንሰር መግለጫ እንዲሁም ግፊት ዲዛይን፣ ሪፖርትና የማጣቀሻ ኮድ፣ የሁሉም ወለሎች የእሳት መከላከያ ፕላን ሪፖርትና መግለጫ እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ
- የእሳት አደጋ ትንታኔና ሪፖርት እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በአዳማ ከተማ እና ጭሮ የፕላን ስምምነት መጠየቅያ ማመልከቻ (ቅጽ 003) እና የግንባታ ፈቃድ መጠየቅያ ( ቅፅ 001) በአግባቡ የማይጠቀሙና ፈቃድ ጠያቂዎቹ ሞልተው ሲያመጡ በፈቃድ ሰጪው መሞላቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፣

መስክ ላይ በተደረገ ቃለ-መጠይቅና ከቀረቡ ዶክመንቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ሚ/ር መ/ቤቱ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ክትትልና ቁጥጥር፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የሕንጻ ሹም አደረጃጀት፣ የይግባኝ ሰሚ ቦርድ እንዲቋቋም..ወዘተ እና ባጠቃላይ የህንጻ አዋጁ እና የህግ ማዕቀፎቹ በክልልችና በከተሞች እንዲተገበር በዕቅዱ መሰረት ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

33. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሰት በቡታጅራና በሀዋሳ ከተሞች የመድህን ዋስትና የማይቀርብ መሆኑ፣

34. በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ክልል በአዳማ፣ በጭሮና በቢሾፍቱ ከተሞች እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ4 ወለልና ከዛ በታች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሰት በቡታጅራ ከተማ ከ3 ወለልና በታች እና በሶማሌ ክልል ከ4ወለልና በታች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በፍኖተ ሰላም (ለአራት ለተፈቀዱ ግንባታዎች) ከተማ የአፈር ምርመራ ሪፖርት እንዲቀርብ ያልተደረገ መሆኑ፣
    - ❖ በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዳማ ከተማ ከG+4 በላይ የሚቀርበው የአፈር ምርመራ ሪፖርት የራሳችን የአፈር ምርመራ ላብራቶሪ ስለሌለ የሚቀርበው ሪፖርት ትክክል ስለመሆኑ እርግጠኛ አለመሆናቸው፣
    - ❖ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በላሊበላ፣ በቆቦ፣ ወልድያ የጸደቁት ዲዛይኖችና ፕላኖች በህንጻ አዋጁ መሰረት አለመሆኑ

- በሶማሌ ክልል አርክቴክቸራል ጥናት ብቻ የሚቀርብ መሆኑ፣ ሆኖም ግን የሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪካል፣ ስትራክቸራል እና ኤሌክትሮ መካኒካል ጥናቶች (ዲዛኖች) የማይቀርቡ መሆናቸው፣
- በመቀሌ ከተማ የሚቀርቡ የጥናት ሰነዶች ተመሳሳይ (ኮፒ) በማድረግ የሚቀርቡ መሆናቸው
- ከሕንጻ አዋጁ አፈጻጸም ጋር ባሉት ክፍተቶች ምክንያት የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ አጥጋቢ አለመሆኑ
- በአፋር ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በትግራይ ክልልና በጋምቤላ ክልል የመንግስት ተቋማትን ጨምሮ ዲዛይንና የሥራ ዝርዝራቸውን ለህንጻ ሹም አቅርበው ዲዛይናቸው ተመርምሮና የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ግንባታ እየገቡ አለመሆናቸው፣
- የትግራይ ክልል ቢሮ የሚያስገነባቸው 121 ፕሮጀክቶች የሕንጻ አዋጁን አሟልተው እንዲተገበሩ አለመደረጉ በቀን 14 ጥር 2010 ዓ.ም በትግራይ፣ በአፋር እና በአማራ ክልል በተደረገ ክትትልና ድጋፍ ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- በቤንሻንጉ ጉምዝ ክልል በአሶሳ ከተማ የመንግስት ግንባታዎች በህንጻ አዋጁ፣ በደንብና መመርያ መሰረት ዲዛይናቸው አለመፅደቁ፣
- የሚጸድቁ ዲዛይኖች ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ ባለቸው መጽደቁ (የስትራክቸራል፣ አርክቴክቸራል፣ የሳኒተሪ እና የኤሌክትሪካል ባለሞያዎች ሳይኖሩ የሚጸድቁ መሆናቸው)፣

በናሙና ከታዩ ከተሞችና ክልሎች እንደዚሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

35. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ሲመልሱ ሚ/ር መ/ቤቱ የግንባታ ፈቃድ በተመለከተ የሚናደርገው ክትትልና ድጋፍ ቢኖርም ሲስተሙን ናሙና በማውጣት እንደሚያዩ ሆኖም ግን የብቃት፣ ጥራት፣ የሰው ኃይል እና የስምምነት ጉዳይ ላይ እኛም ጋር ችግር ያለ መሆኑ፣ በድጋፍና ክትትል ይህን ለመስራት የሚከብዳቸው መሆኑ እና ውስንነቶች ያሉ መሆኑና ወደፊት የሚስተካከል መሆኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

36. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የኮንስትራክሽን ኦዲት በ2010 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ተደርጎ ያሉ ክፍተቶች ለማሳወቅ እንደተሞከረ በተለይ የኤለክትሪካል፣ ሳኒተሪ፣ ስትራክክቸራል እና ሌሎችም ቴክኒካል ምርመራዎች ሰፊ ጊዜና እውቀት የሚጠይቁ በመሆናቸው ይህን ታሳቢ በማድረግ ከክልሎች ለተውጣጡ 80 ባለሞያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ኦዲት በማድረግ ግብረመልስ የተሰጠ መሆኑ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት ገልጸዋል፡፡

37. የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በክልልና በከተሞች እየተገነቡ ያሉ ሕንጻዎች አዋጁን ተከትለው የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ በዕቅዱ መሰረት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ የተሰጠው ግብረ-መልስ በዕቅዱ መሰረት አለመሆኑና ከ2008 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ችግሮቹ ተመሳሳይ መሆናቸውና ያልተስተካከሉ መሆናቸው፣ በተጨማሪም ለአዲስ አበባ ከተማ የተደረገው የኮንስትራክሽን ኦዲት ሪፖርት ግብረመልስ እንደሰጡ ቢገልጹም ኦዲት ሲደረግ የተስተካከለ ስለመሆኑና ሪፖርቱ ስለመስተካከሉ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ከክልል ለተውጣጡ 80 ባለሞያዎች ተሰጠ የተባለው የአሰልጣኞች ስልጠና ስለመቅረቡ ማስረጃ ስላልቀረበ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

38. ሚ/ር መ/ቤቱ በሀገሪቱ የሚገነቡ ሕንጻዎች የግንባታ ፈቃድ አግኝተው እንዲገነቡ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ ከሆነ የሚገነቡ ህንጻዎች የህዝብን ጤንነትና ደህንነት የጠበቁ እንዳይሆኑ እና በሀገሪቱ ምቹ የግንባታ ሥርዓት ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚያደርግ ሲሆን የህንጻ አዋጁን እና ሌሎች የኮንስትራክሽን የህግ ማዕቀፎችን ተፈጻሚ እንዳሆን ያደርጋል፡፡

## የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ያገኘ መሆኑ

39. በክልሎችና በከተሞች ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛው ሰው የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ሊያገኝ ይገባል፡፡ ሚኒስቴርር መ/ቤቱ ይህ መደረጉን የሚከታተልበትን ሥርዓት ዘርግቶ በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡

40. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ ከተሞችና ክልሎች፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ለማግኝት የፕላን ስምምነት የሚሰጠው በማዕከል ሳይሆን በክፍለ ከተማ የሚጸድቅ መሆኑ፣ የፕላን ስምምነት አሰጣጥ ወጥ አለመሆንና
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ፣ በአዳማና በቢሾፍቱ ከተሞች የግንባታ ፈቃድ የከተማ ፕላን ለተዘጋጀላቸው የፕላን ስምምነቱ በከተማው መሪ ፕላን ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የተረጋገጠ ሆኖ ዲዛይን እየተደረገ አለመሆኑ፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባህር ዳር ከተማ የፕላን ስምምነት ሳይኖር ግንባታዎች የሚገነቡ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ ቢሾፈቱ፣ በፍኖተ ሰላምና በባህር ዳር ከተሞች ህንጻዎች የግንባታ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የፕላን ስምምነት ያገኙ ስለመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆኑ ክልሎች ክትትልና ድጋፍ ያላደረጉ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ ከተማ በናሙና ካየናቸው በ2010 ዓ.ም ከተሰጡ 7 የግንባታ ፈቃድ ውስጥ 7ቱም በፈቃድ ጠያቂዎች ሞልተው ሲያመጡ ፈቃድ ሰጪው የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ (ቅፅ 003) መሞላቱን የማያረጋግጥ መሆኑ፣ የፕላን ስምምነቱ በሚመለከተው ኃላፊ ተፈርሞ እና በመ/ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለተጠየቀው አካል ያልተሰጠ መሆኑ፣

41. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው ነበራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ምንም ምላሽ አልሰጡም፡፡

42. በክልሎችና በከተሞች የሚካሄዱ ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት የማያገኙ ከሆነ ህገወጥ ግንባታዎች እንዲስፋፉ፣ መሬትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል፣ ክልላዊ ወይም ከተማ ነክ አጠቃላይ የፕላን ድንጋጌዎች እንዳይመራ እና ለነዋሪውና ህብረተሰቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የሚሰጡ ህንጻዎች በከተማው መሪ ፕላን የተቀመጡ የህንጻ አጠቃቀሞችን፣ ከፍታዎችንና የሰፈር ወይም የአከባቢ ፕላን ገፅታዎችን መሰረት ያደረገ ፕላን እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

## በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካልጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ

43. በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ የሚከታተልበትን እና የሚደግፍበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች (አዲስ አበባና ድሬዳዋ) እና ሦስት ክልሎች (በአማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ)፡-

- ✓ በአዲስ አበባ ናሙና በመምረጥ ካየነው 36 የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የሕንጻ ግንባታዎች ተዳፋት (Ramp)ና የምድር ወለል (Ground Floor) ብቻ የሚያስገድዱ መሆኑ፣
- ✓ በድሬዳዋ ከተማ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በጭሮ፣ በአዳማና በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፍኖተ ሰላምና በባሕር ዳር ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቡታጅራና በሀዋሳ ከተሞች የሕንጻ ግንባታዎች ተዳፋት (Ramp)ና የምድር ወለል (Ground Floor) ብቻ የሚያስገድዱ መሆኑ፣
- ✓ የየወለሉ መዳረሻዎች ለአካል ጉዳተኞች የተመደቡ የመኪና ማቆምያዎች፣ የየወለሉ ለአካል ጉዳተኞች የሚመቹ መጸዳጃ ቤቶች ዲዘይን ተደርጎ የማይጸድቅ መሆኑ፣
- ✓ በሕዝብ መገልገያ ሕንጻ ውስጥ የመሰብሰብያ አዳራሽ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረግ የማይጸድቅ መሆኑ፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕንጻ ዲዛይኖች የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነትን ያካተቱ እንዲሆን ያደረገው ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ
- ✓ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ አዲስ አባባ ከተማ አስተዳዳር ትምህርት ቢሮ፣ ብሔራዊ ባንክ፣ የአዲስ አባባ ሲኒማ ቤት፣ ዮኒቨርሳል ቴክኖሎጂ ኮሌጅ፣ ዳሽን ባንክ፣ (5 ኪሎ ያለው)፣ የአዲስ አባባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ ሬጀስትራር፣ አዲስ አበባ ኮሜርስ ኮሌጅ ሬጅስትራር፣ አዲስ አባባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ብሔራዊ ትያትር፣ ብሔራዊ ሙዝየም እና የቤት-መጻህፍትና ቤተ መዛግብት አካል ጉዳተኞች ተደራሽ ያላደረጉ መሆኑን የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበር የገለጹ መሆናቸው፣

- ✓ የቀድሞ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑ ለአካል ጉዳት ፌዴሬሽን በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ላይ የገለጹ መሆናቸው፣
- ✓ የቀድሞው ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕንጻ ዲዛይኖች የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነትን ያካተቱ እንዲሆን ያደረገው ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ፣

45. የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው እና የአይነስውራን ብሔራዊ ማህበራት በቀረበ መጠይቅ፡-

- ✓ በአዲስ አባባ ከተማ በትህምርት ቤት፣ በገብያ ማዕከል፣ በአምልኮ ቦታ፣ በመንግስት ተቋማት እና በግል ተቋማት አካል ጉዳተኛ ተደራሽ ያላደረጉ ህንጻዎች ያሉ መሆኑ፣
- ✓ በሚሰሩበት ተቋም አካል ጉዳተኛ ተደራሽ መሟላት ካለበት ውስጥ ራፕ፣ መጸዳጃ ክፍል፣ መስብሰብያ አዳራሽ፣ የመኪና ማቆሚያ እና ሊፍት ያልተሟሉ መሆኑ፣
- ✓ በተጨማርም የሚሰሩ እና እየተሰሩ ያሉ ተዳፋት (Ramp) ደረጃውን የጠበቅ አለመሆኑ፣
- ✓ አብዛኛውን ጊዜ ህንጻዎች የሚገነቡት የአካል ጉዳተኞችን ያማከሉ አለመሆናቸው፣
- ✓ መስማት ለተሳነቸው ወዴት መሄድ እንዳለባቸው የሚያመለክት ቋንቋ የሚገልፀ ምልክት የሌለው መሆኑ፣
- ✓ በመንግስት ሆነ ማንኛውን ድርጅት ህንጻዎች የአካል ጉዳተኞች በተሟላ ሁኔታ ያማከሉ አለመሆናቸው፣

ገልጸዋል፡፡

46. በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና 47 ግንባታዎችን በመምረጥ ከተከለሱ ሰነዶች ውስጥ የመጠቀሚያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሕንጻዎች፡-

- ✓ ተዳፋት (Ramp)ና የምድር ወለል (Ground Floor) ብቻ የሚያስገድዱ መሆኑ፣
- ✓ አካል ጉዳተኞችን በየመዳረሻዎቹ ከዕንቅፋት የሚጠብቁቸው እንዲሁም በየወለሉ በመኪና ማቆምያነት የተያዙላቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ጀረጃ ያለቸው ምልክቶች ያልተደረጉ መሆኑ፣
- ✓ ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር ባላይ ከፍታ ያለው ምንኛውም ህንጻ የአሳንሰር ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖረው እና አሳንሳሮቸም ያለመቋረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ያልተደረገ መሆኑ

- ✓ ለአካል ጉዳተኞችን የሚያመች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ከአመቺ መዳረሻ ጋር የሌለው መሆኑ
- ✓ የመሰብሰብያ አዳራሹ በተሽከርካሪ ወንበር ወይም በክራንች ለሚንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኞች ታሳቢ ያደረገ የመቀመጫ ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት አለመሰራቱን
- ✓ በፋብሪካዎች፣ በትምህርት ተቋማት፣ በማምለኪያ (አምልኮ) ቦታ እና በገብያ ማዕከል ለአካል ጉዳተኞ የሚያመች የልብስ መቀየርያና የመጸዳጃ ክፍል መዘጋጀቱ ተረጋግጦ የማይሰጥ መሆኑ
- ✓ ለአካል ጉዳተኛ የሚያመች መጸደጃ ቤቶች የተዘጋጁ መሆኑ የማይረጋገጥ መሆኑ
- ✓ በአዲስ አበባ 26 ሕንጻዎች፣ በድሬዳዋ 12 ሕንጻዎች፣ በጭሮ 11 ሕንጻዎች፣ በአዳማ 14 ህንጻዎች፣ በቢሾፍቱ 12 ሕንጻዎች፣ በቡታጅራ 10 ሕንጻዎች፣ በሀዋሳ 14 ሕንጻዎች፣ በፍኖተ ሰላም 14 ሕንጻዎች እና በባህር ዳር 16 ሕንጻች ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ሲሰጥ እና ቋሚ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ ከ4ኛ ፎቅ በታች ለአገልግሎት ተደራራሽ የሆኑ የተመቻቸ ሁኔታ በሌለበትና ከ4ኛ ፎቅ በላይ ለሚኖረው የሕዝብ መገልገያ ሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኛ የሚያመች አሳንሰር በሕንጻው ውስጥ መገጠሙ ሳይረጋገጥ የሚሰጥ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

47. በአካል የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው በአዲስ አባባ ከተማ 21 ህንጻ፣ ድሬዳዋ 13፣ በጭሮ 11፣ በአዳማ 18፣ በቢሾፍቱ 40፣ በቡታጅራ 10፣ ሀዋሳ 20፣ በፍኖተ ሰላም 20፣ በባህር ዳር 28፣ በድምሩ 181 ሆቴሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒክ፣ የአምልኮ መስጫና የንግድ አገልግሎት ህንጻዎች ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁና በከፊል ያልተጠናቀቁ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸውና ያልተሰጣቸው ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ አለመሆናቸው ታውቋል፡፡

- ✓ በከፊል የተጠናቀቁ የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሲፈለግ መሟላታቸውን ከሚያረጋግጡ ሁኔታዎች አንዱ ለአካል ጉዳተኞኞ የሚያመቹ መሆናቸው ተረጋግጦ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ውስጥ አካል ጉዳተኞችን በየመዳረሻዎቹ ከዕንቅፋት የሚጠብቋቸው እንዲሁም የየወለሉ በመኪና ማቆምያነት የተያዙላቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለቸው ምልክቶች መደረጉ የማይታይ መሆኑ፣

- ✓ በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንጻ ውስጥ የሚገኝ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተሽከርካሪ ወንበር ወይም በክራንች ለሚንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኞች ታሳቢ ያደረገ የመቀመጫ ቦታ በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱ ተረጋግጦ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ በፋብሪካዎች፣ በትምህርት ተቋማት፣ የማምለኪያ ቦታዎች እና የገበያ ማዕከላት ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የልብስ መቀየርያና የመጸዳጃ ክፍል መዘጋጀቱ ተረጋግጦ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ በየወለሉ ለአካል ጉዳተኞች የሚመቹ መጸዳጃ ቤቶች የተዘጋጁ መሆናቸው ተረጋግጦ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ጊዚያዊ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ ከ4ፎቅ በታች ለአገልግሎት ተደረራሽ የሆነ የተመቻቸ ሁኔታ በሌለበትና ከ4ፎቅ በላይ ለሚኖረው የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች አሳንሰር በሕንጻ ውስጥ መገጠሙ ተረጋግጦ የማሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር በላይ ከፍታ ያለው ማንኛውም ህንጻ የአሳንሰር ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖረው እና አሳንሰሮቹም ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዲሰጥ የሕዝብ መገልገያ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ከአመቺ መዳረሻ ጋር የተዘጋጀ መሆኑ ሳይረጋገጥ የሚሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ባብዛኛው ሕንጻዎች ሲገነቡ የሚሰሩ ተዳፋት (Ramp) የሚያንሸራትቱ፣ ምቹ ያልሆኑ በሌላ ቁስ የተሸፈኑ ሆነው የተሰሩ መሆናቸውና አለማቀፍ (የሕንጻ አዋጁን መሰረት) ተደርጎ ያልተሰራ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡




**በአዲስ አበባና በድሬዳዋ አካል ጉዳተኞችን ያላማከለ መጸዳጃ ቤት እና ተዳፋት(Ramp) የሌላቸው ሕንጻዎች**



**በአዲስ አበባ ባለ ስድስት ፎቅ ህንጻ ሊፍቱ ሳይገጠም ቋሚ የመጠቀሚያ ህንጻ የተሰጠው**

48. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ በሆሳዕና፣ በሻሸመኔ፣ መቀሌ፣ አላማጣ፣ ቆቦ፣ መርሳና ወልድያ ከተሞች፣ በሀረሪ፣ በአፋር፣ በኢትዮ ሶማሌ፣ በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ከተሰጡ የሕንጻ ግንባታዎች ተዳፋት (Ramp)ና የምድር ወለል (Ground Floor) ብቻ የሚያስገድዱ መሆኑ፣
- ✓ በአፋር ክልል የዲዛይን ማጸደቅ ሂደት ላይ ለአካል ጉዳተኞች ከግምት ውስጥ የማያስገቡ መሆኑ ተደራሽ አለመሆኑ በሰኔ 2009 ዓ.ም በተደረገ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ላይ መገለጹ፣

- ✓ በጅማ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ሲሰጥ (ደረጃ ሐ) አካል ጉዳተኛን ባገናዘበ መልኩ ያለመሆኑ በሚገነቡ የግንባታ ውጤቶች የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚና ተደራሽ ያለመሆን በሰኔ 2009 ዓ.ም በተደረገ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ላይ መገለጹ፣
- ✓ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ምልከታ በህንጻ አዋጁ መስፈረት መሠረት የሚገነባው ህንጻ ለአካል ጉዳተኞች ታሳቢ ያደረገ መጸዳጃ ቤት ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑ በ2010 በጀት ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ላይ መገለጹ፣
- ✓ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚቀርቡ የደረጃ "ሐ" ህንጻ ዲዛይኖች በሚገመገሙበት ጊዜ በህንጻ አዋጁ መሠረት ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት በመስጠት ራምፕ፣ ሊፍት ውስጥ በተገቢው ሁኔታ መካተታቸውን እንዲረጋገጥ የሚመደረግ ቢሆንም አካል ጉዳተኞች ታሳቢ ያደረገ መጸዳጃ ቤት በዲዛይን እንዲካተት ከማድረግ አንጻር አዋጁ በሚያስቀምጠው ልክ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት አለመሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡
- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ የሕንጻ ዲዛይኖች የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነትን ያካተቱ እንዲሆን ያደረገው ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. ስለጉዳዩ የክልልና የከተሞች የስራ ሃላፊዎች ተጠይቀው ለየሕንጻ ምድቡ የሚዘጋጁ ፕላኖች (ዲዛይኖች) ሲዘጋጁ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ ሆነው የማይዘጋጁ መሆኑና የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን እንደማይታይ እና ተዳፋት (Ramp) ብቻ የሚያስገድዱ መሆኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

50. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የተጠየቀው ጥያቄው ልክ እንደሆነ፣ እየተሰራ እንዳልሆነ እንዲሁም ከዲዛይን ማጽደቅ ጋር የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር መጸዳጃ ቤቶች ጋር በተገናኘ በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይን የሚጸድቁ መሆኑ፣ በጸደቀው ዲዛይን መሰረት እየተሰራ እንዳልሆነ በግንባታ ወቅት ግን ከክትትልና ቁጥጥር ችግር ያለ መሆኑን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ወቅት ገልጸዋል፡፡

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገነቡ ሕንጻ ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኛ፣ ለአረጋውያን የሚመቹ ወይም የእነሱን ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያስገባ ፍታዊ ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳትፎአቸውን ከግምት ውስጥ ገብቶ ዲዛይን የማይሰራና ግንባታቸውም ይህን

ባገናዘበ መልክ የማይከናወን ከሆነ በሕንጻዎቹ ሚሰጡ አገልግሎቶች እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዳሆኑ ያደርጋል፡፡

**በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን በተመለከተ**

52. ሚ/ር መ/ቤቱ በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሦስቱም ክልሎች እና ሁለቱ ከተማ መስተዳደሮች ያሉ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሂደትን ተከትለው የማይሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡፡-

54. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልልና ከተሞች የኮንስትራክሽን ቢሮዎችና ባለሥልጣኖች

- ✓ ሕንጻዎች በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፋቸው የመከታተያ ደብተር የማይያዝ መሆኑ፣ ክትትልና ቁጥጥሩ በማንኛውም ሰዓት ገብተው የማያደርጉ መሆኑ፣ በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ በግንባታ መከታተያ ቅፅ 013 በመሙላት ለሕንጻ ሹም የማይቀርብ መሆኑ፣
- ✓ ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለሚደረግ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- ✓ ለግንባታ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን በዓይን ከማየት ውጭ የግንባታ መከታተያ ላብራቶሪ የሌለ በመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑ፣
- ✓ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ለግንባታ ግብዓት የሚውሉ ቁሳቁሶች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ለግንባታ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች (ግብዓቶች) በሕንጻ ሹም የጥራት ማረጋገጭ የማይደረግባቸው መሆኑ፣
- ✓ ክትትል የሚያደርገው ባለሞያ ሥራው ወደተጠናቀቀ ወይም በግንባታ ላይ ወደሚገኝ ህንጻ የገባ ተቆጣጣሪ ስለገባበት ዓላማ እና ስለተመለከተው ሁኔታ በግንባታ መረጃ መዝገብ ላይ የማያሰፍሩ መሆኑ፣
- ✓ የሕንጻ ሕጎቹን በመተላለፍ ግንባታ ለፈጸሙ የማስቆሚያ ትዕዛዝ ለመስጠት (ቅፅ 015) የማይሞሉ መሆኑ፣

- ✓ ለማንኛውም ግንባታ የቁጥጥር ክፍያ የሚፈጸመው ቁጥጥር የሚደረግበትን የሥራ እርከን ለማስጀመር ገንቢው የግንባታ ሥራ ማስታወቅያ (ቅፅ 025) የማይሟላ መሆኑ፣
- ✓ በክልሎችና በከተሞች ግንባታ ፈቃድ ከመስጠት ባለፈ በህንጻ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር የማደረግ መሆኑ፣
- ✓ በአዲስ አበባ ከ2008 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ 216 ህንጻዎች፣ በድሬዳዋ ከተማ 11፣ በጭሮ ከተማ 11፣ አዳማ 15፣ በቢሾፍቱ 12 ህንፃዎች፣ በቡታጅራ 10 በሀዋሳ 18፣ በፍኖተ ሰላም 15 እና በበህርዳር ከተማ 24 ህንጻዎች በሕንጻ አዋጁ መሰረት በክትትልና ቁጥጥር ሂደት ያላለፉ መሆናቸው፣

ታውቋል፡፡

55. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በሻሸመኔ፣ በለቀምትና በመቱ ከተሞች፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በላሊበላ፣ በቆቦና በወልድያ ከሚሴ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሆሳና እና በሸኖ ከተሞች፣ በአፋር ክልል፣ በሀረር ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልና በትግራይ ክልል የመንግስት የሕንጻ ግንባታዎችና የግለሰቦች ሕንጻዎች ሲገነቡ በሕንጻ አዋጁ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገላቸው የማይገነቡ መሆኑ፤

56. በተጨማሪም፡-

- በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ በኦሮሚያ ክልል ለጭሮ፣ ለአዳማ፣ ለቢሾፍቱ ከተማ፣ በደቡብ ክልለ ለቡታጅራና ለሀዋሳ ከተማ፣ በአማራ ክልል ለፍኖተ ሰላምና ለባሕርዳር ከተሞች መቐለ፣ አላማጣ፣ በጋምቤላ፣ አፋር፣ ኢትዮ ሶማሌ፣ሀረሪና ቢንሻንጉል ጉምዝ ከተሞች ህገ-ወጥ ግንባታዎችን ለማስቆም ለደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ደብዳቤ ከመጻፍ ያለፈ ስራ የማይሰራ መሆኑ
- በአማራ ክልል በባሕር ዳር ከተማ ያለ ግንባታ ፈቃድ፣ ፕላን ስምምንትና ዲዛይን ሳይጸድቅ መገንባት፣ ለመኪና ማቆሚያ የተሰራውን ቤዝመንት ለሌላ አገልግሎት ማዋል፣ ሴት ባክ (ወሰን ሳይጠብቁ) መገንባት፣ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በተለያዩ ቦታዎች የሚያስገነባቸው ሕንጻዎች ያለግንባታ ፈቃድ መሆናቸው፣ በዲዛይን መሰረት ሊፍት አለመስራት፣ በዲዛይን መሰረት ቤዝመንቱን ድፍን

አድርጎ መስረት (ያለ አክሰስ) መስራት፣ መጸዳጃ ቤት በሕንጻ አዋጁ መሰረት አለመስራቱ፣

- በአፋር ክልል በሕንጻ መመሪያው መሰረት የቁጥጥር ስራ አለመደረጉ እንዲሁም ያልጸደቀ (የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው) ሕንጻዎች የሚገነቡ መሆኑ፤
- በአፋር ክልል የሚገነቡ የግንባታዎች ቁጥጥርና ውለታ አስተዳደር የስራ ሂደት ዲዛይን ተድርጎ የተገነቡ 39 ግንባታዎች በሙሉ በአዋጁ መሰረት አለመሆኑ፣ በባህር ዳር መቀሌ እና ሰመራ ከተሞች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ስራ ሪፖርት ላይ የተጠቀሰ መሆኑ
- በላሊበላ፣ ወልድያ ከተማ የህንጻ ዲዛይኖች እና ግንባታዎች የወሰን ርቀትን ሳይጠብቁ የሚሰሩ መሆኑ፣
- በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ ደቡብ ጎንደር፣ በሰሜን ወሎ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ በአማራ ክልል ኦሮምያ ዞን፣ መአከላዊ ጎንደር ዞን  በደቡብ ወሎ፣ አዊ ዞን ከተሞች የግንባታ ፈቃድ ሳይኖራቸው ግንባታዎች እየተሰሩ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 18 ሕንጻዎች ወሰን ሳይጠብቁ መገንባት፣ 48 ሕንጻዎች የአፈር መንሸራተት መከላከያ ሳይሰሩ ግንበታ መጀመር፣ በትርፍ ከይዞታ ማረጋገጫ ካለው በተጨማሪ መስራት፣ በግንባታ ወቅት መደረግ የነበረበት ጥንቃቄ ሳይደረግ መገንባት፣ ከባለስልጣኑ ዕውቅና ውጪ ግንባታ አስፋፍተው መገንባት፣ የዲዛይን ለውጥ በማድረግ መገንባትና እና  ከተፈቀደው ውጪ ወለል በመጨመርና በመቀነስ የሚገነባ መሆኑ፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡





በባህርዳርና በድሬዳዋ ከፕላን ውጭ ወለል በመጨመር የተሰሩ ህንጻዎች

57. ስለጉዳዩ በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮችና (አዲስ አበባና ድሬዳዋ) እና በሦስቱ ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ደቡብና አማራ) የሚገኙ የህንጻ ሹሙ ኃላፊዎች፣ የኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎች እና የስራ ሂደቶች በከተማው የሚገነቡ ህንጻዎች ባለው የሰው ኃይል እጥረት፣ በሎጅስቲክና በበጀት እጥረት ምክንያት የግንባታ ፈቃድ ወስደው የሚገነቡትን ሁሉንም ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑና በተወሰኑት ላይ ብቻ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በአዋጁ መሰረት ቅጣት በመቅጣትና ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ ሌላ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ፣ በመስክ ምልከታና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- የሕንጻ ግንባታ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም
- ችግሩን ከማየትና ደብዳቤ ከመጻፌ ዉጭ ሌላ ያደረግነው ነገር የሌለ መሆኑ፣
- ይህ ግኝት እኛም በክትትልና ቁጥጥር ጊዜ ያገኘነው ግኝት ሲሆን በግብረ መልስ ለክልሎችና ለከተሞች የላኩ መሆናቸውን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

59. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባደረገው ድጋፍና ክትትል ስራዎች የተገኙ ግኝቶች ለክልሎች እንዲስተካከሉ ግብረ-መልስ የተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ምላሽ ቢሰጥም ከ2008 እሰከ 2011 ዓ.ም ድረስ በህንጻዎች ላይ የሚታየው ችግር ተመሳሳይ መሆኑና በግብረ መልሱ መሰረት

ማስተካከላቸውና አለማስተካከላቸው ክትትል ያላደረጉና ችግሮቹ ያልተስተካከለ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

61. በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች በክትትልና ቁጥጥር ሂደት እንዲያልፉ አለመደረጉ ለህዝብ ጤንነትና ደህንነት አስጊ ከመሆኑም የተነሳ ሀገሪቱ ለከፍተኛ ወጪ እንድትዳረግ ያደርጋል፣ ህገወጥ ግንባታዎች እንዲስፋፉ፣ የተገነቡት ሕንጻዎች ቢሆንም የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው የተገነቡ መሆናቸው ጥርጣሬ ውስጥ ማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች አገልግሎት መስጠት ከመጀመራቸው በፊት የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን በተመለከተ

62. ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞችና በክልሎች በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሂደት ተከትለው እየተሰጣቸው መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ናሙና በመምረጥ ባየናቸው፡-

- የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጡ ከተሞች በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ መስፈርት ማሟላታቸው ሳይረጋገጥና ሂደቱን ሳይከተሉ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2010 ዓ.ም ከተሰጡ የመጠቀሚያ ፈቃድ ከተሰጣቸው 47 ህንጻዎች ውስጥ 47ቱም፣ በድሬዳዋ ከተሰጡት 3 ህንጻዎች ውስጥ 3ቱም፣ በቢሾፍቱ 4 ህንጻዎች ውስጥ 4ቱም፣ በአዳማ 3 ሕንጻዎች ውስጥ 3ቱም፣ በሀዋሳ 6 ህንጻዎች ውስጥ 6ቱም፣ በባሕርዳር 4 ህንጻዎች ውስጥ 4ቱም ሂደቱን ተከትሎ ያልተሰጣቸው መሆኑ፡-
- በሕንጻው ባለቤት እና በፈቃድ ሰጪው የመጠቀምያ ፈቃድ በማመልከቻ (ቅፅ 018) የማይሞላ መሆኑ፣
- ግንባታው መጠናቀቁን የሚረጋግጥበት አማካሪ መሐንዲስና የሕንጻው ባለቤት የተፈራረሙበት የርክክብ ሰነድ ስለመኖሩ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፣
- ሕንጻዉ በፕላኑ ስለመሰራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠው ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ በፍተሸ የሚረጋገጠው በአርክቴክቸራል ክፍል ብቻ መሆኑ፣ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው፣ አምስት እና ከዛ በላይ ያሉ ሕንጻዎች ሁለት መወጣጫ ደረጃ ሊኖራቸው ሲገባ ነገር ግን አንድ መወጣጫ ደረጃ ብቻ እንዲኖር የሚደረግ መሆኑ አንድ ብቻ የአደጋ ጊዜ መውጫ መኖር፣ የአደጋ ጊዜው መውጫው በሮች የሚቆለፉ መሆኑ፣ የተገጠሙ ሊፍት በየጊዜው የሚበላሽ መሆኑ፣ ሊፍቶች የሚገጠሙበት ሥፍራ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆን፣ በብዛት ሊፍት ያልተገጠመላቸው እንዲሁም የመኪና ማቆሚያ (ፓርኪግ) ለሌላ አገልግሎት (ለባንክ አገልግሎት እንዲውል፣ ለህክምና አገልግሎት፣ ለክሊኒክ፣ ለጭፈራ ቤት ለእስቶር፣ በከፊል ለእንጀራ መጋገርያ፣ ለሱፐር ማርኬት ወዘተ.. እንዲሁም ምንም አገልግሎት እንዳይሰጥ የሚደረጉ መሆናቸው) የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው ህንጻዎች መኖራቸው፣
- የህንጻዎች መግቢያ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆን፣
- በየወለሉ የእሳት አደጋ መከላከያ ያልተገጠመ መሆኑ፣ የእሳት አደጋ መከላከያው ለአጠቃቀም ምቹ እንዲሆን ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- የባለመስታወት ግድግዳ ለሚገጠምላቸው ሕንጻዎች ነጸብራቁ በነዋሪው ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑ የሚረጋገጥበት አስራር ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣ እና መጠቀሚያ ፈቀድ ሲሰጥ የማይታይ መሆኑ፣
- በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ ጋር የሚቀርብ ሰነዶች ለክትትልና ቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ ተያይዞ ያልቀረበ መሆኑ፣ የፕላን ማሻሻያ ወይም ለውጥ ከተደረገ የተሸሻለውን አካቶ የተዘጋጀ ወይም የተከለስ ፕላን ቅጂ እንዲኖረው ቢደረግም የማሻሻያ የተደረገበት የግንባታ ፈቃድ የሌለው መሆኑ፣
- ከዲዛይን ውጭ የተሰራን በመቅጣት ማሻሻያ ተሰጥቶት መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጠው መሆኑ፣
- ለአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆምያነት የተያዙላቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ጀረጃ ያላቸው ምልክቶች የማይደረግ መሆኑ፣
- **በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር** በናሙና የታዩ 9 (የንግድ አገልግሎት፣ ትምህርት ቤትና ሆስፒታሎች) ሕንጻዎች ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁና እና 9 (የንግድ አገልግሎት፣ የባንክ፣ ትምህርት ቤትና ሆስፒታሎች) ሕንጻዎች

በከፊል የተጠናቀቁ ህንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት እሰጡ መሆናቸው እና 9 ሕንጻዎች የመኪና ማቆምያ ቤዝመንቱን ለሌላ አገልግሎት የተጠቀሙ መሆናቸው፣

- **በበድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፡** በከፊል የተጠናቀቁና ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁ 11 ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸውና ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ ሳይሆኑ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው፣ 2 ህንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊው መዳረሻ ተዳፋት አለመኖር፣ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌለው መሆኑ፣
- **በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡-**
    - በጭሮ ከተማ ሕንጻ ሹም ከተቋቋመ ጀምሮ ምንም ዓይነት የመጠቀሚያ ፈቃድ ያልተሰጠ መሆኑ፣ እንዲሁም 11 ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸውና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሳይሆኑ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ መሆናቸው፣
    - በአዳማ ከተማ 15 (ሆቴሎች፣ የንግድ ማዕከላት፣ እንግዳ ማረፍያና ትምህርት ቤት) ህንጻዎች በከፊል የተጠናቀቁና ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁ ህንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ፣ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሳይሆኑና የአደጋ ጊዜ መውጫ ሳይኖራቸው አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውና የአደጋ ጊዜ መውጫው ዝግ መሆኑ፣
    - በቢሾፍቱ ከተማ 34 (ሆቴሎች፣ የንግድ ማዕከላትና ቢሮዎች) ህንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው፣ ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ አለመሆኑ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌለው መሆኑና ሊፍት የሌላቸው መሆኑ፣ የእሳት አደጋ ለአጠቃቀም ዝግጁ ሆኖ አለመለጠፉ፣ የእሳት አደጋ መከላከያው ጊዜ ያለፈበት መሆኑ፣
- **በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል**
    - በቡታጅራ ከተማ የህንጻ ሹም ከተቋቋመ ጀምሮ ምንም ዓይነት የመጠቀሚያ ፈቃድ ያልተሰጠ መሆኑ፣ 10 ሕንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው፣
    - በሀዋሳ 18 ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸውና ለአካል ገዳተኞች ተደራሽ አለመሆናቸው፣ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው መሆኑና አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው፣

- በአማራ ብሔራዊ ክልል፡-
  - በፍኖተ ሰላም ከተማ የህንጻ ሹም ከተቋቋመ ጀምሮ ምንም አይነት የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ያልተሰጠ መሆኑ፣ በፍኖተ ሰላም 20 (ሆቴሎች፣ ዕንግዳ ማረፍያ፣ የንግድ አከልግሎት ሆስቢታሎች፣ ቢሮዎችና ወዘተ....) ሕንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት እየሰጡና የሕንጻ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ያልተገነቡ መሆኑና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆናቸው፣
  - በባህርዳር ከተማ በ2008 ዓ.ም እና በ2009 ዓ.ም ምንም መጠቀሚያ ፈቃድ ያልተሰጠ ሲሆን በ2010 ዓ.ም ለ6 ህንጻዎች ብቻ የመጠቀሚያ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ፣ የተሰጠውም መጠቀሚያ ፈቃድ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሂደትን ተከትሎ የተሰጠ አለመሆኑ እንዲሁም ካየናቸው 24 ህንጻዎች ውስጥ 24ቱም ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው

በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡






**በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐዋሳ ከተሞች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ ተጠናቀውና በከፊል የተጠናቀቁ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ህንጻዎች**

64. በተጨማሪም

**በአዲስ አበባ፡-**

- 51 ህንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣
- 66 ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ ኖሯቸው ነገር ግን አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ አገልግሎት የሚሠጡ መሆናቸው (ሊፍት ሳኖራቸው፣ እሳት አደጋ መከላከያ ሳይገጠምላቸው፣ ከተፈቀደው ግንባታ ውጪ ወለል በመጨመር፣ አደጋ በሚያደርስ መልኩ በውስጥና በውጭ የማጠናከርያ ስራዎችን በመስራት አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው) እና
- 37 ህንጻዎች ለመኪና ማቆምያ ፓርኪንግ የተፈቀደውን ቤዝመንት ለሌላ አገልግሎት (ለስቶር፣ ለባንክ ማከራየት፣ በከፊል ለሌላ አገልግሎት፣ ለመጋዘን አገለግሎት እንዲውል) መደረጉ፣
- **በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡-** የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በሻሸመኔ ከተማ፣ በጅማ፣ በለቀምትና በመቱ ከተሞች ከመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በከተማውና በክልል ውስጥ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸው እንዲሁም ከተፈቀደላቸው ውጭ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ህንጻዎች መኖራቸው እና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣
- **በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፡-** የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በሆሳዕና በሸኖ ከተሞች ከመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በከተማውና በክልል ውስጥ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸው

እንዲሁም ከተፈቀደላቸው ውጭ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ህንጻዎች መኖራቸው እና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣

- **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡-** በወልድያ፣ በላሊበላ፣ በከሚሴ ከተሞች በከተማውና በክልል ውስጥ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸው እንዲሁም ከተፈቀደላቸው ውጭ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ህንጻዎች መኖራቸው እና በከፊል የተጠናቀቁ ሕንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣
- በአፋር ክልል፣ በሀረሪ ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልና በትግራይ ክልል ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቁና በከፊል የተጠናቀቁ ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ የማይሰጥ መሆኑ እና ያላለቁ ህንጻዎች አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣

ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩ የክልሎቹ እና የከተሞቹ የኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎች፣ የሕንጻ ሹም ኃላፊዎች እና የስራ ሂደቶች ተጠይቀው

- የመጠቀሚ ፈቃድ ሳይኖራቸው አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች ያሉ መሆኑ በተለይም ያላለቁ ህንጻዎች ላይ አገልግሎት መስጠት እንደ ሀገር ችግር የሆነ መሆኑ፣
- ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች እንዲኖር ያደረገው አንድ በቅንጀት የመስራት ሥራዎች ደካማ በመሆኑ እና በቂ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደገ መሆኑ፣
- ክትትልና ቁጥጥር ስላልተደረገባቸው የመጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑ፣
- ግንባታቸው በከፊል እና ሙሉ በሙሉ ለተጠናቁ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጣቸው ሂደቱ ተከትለውና በዲዛይኑ እና ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉት እስታንዳርዶች መሰራት በፍተሽ ሳይረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑ፣
- የመንግስት ህንጻዎች ጨምሮ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖራቸው አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች በአዲስ አበባ ያለ መሆኑ፣
- ህንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖራቸው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የሚደርገው የኢኮኖሚ ችግር መሆኑ ባለሀብቱ ከስር እያከራየ ሌላውን ለመጨረስ እና ከባንኮች በብዛት ብድር ስለሚወስዱና እነሱ የሚከራዩት ለ5

ዓመት ስለሆነ እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ በተመለከተ አሰራሩ ግልጽ ያልሆነላቸው መሆኑ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

66. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው እንደሚኒስቴር መ/ቤት ያደረግነው ነገር የለም፤ ክትትል ሳይደረግ የመጠቀሚያ ፈቃድ እንደሚወስዱ እንደሚያዉቁ እና ምንም ያደረጉት ነገር እንደሌለ፤ ውይይት ከማድረግ ውጪ ሌላ ነገር አለማድረጋቸውን እንዲሁም ምንም የተሰራ ነገር እንደሌለ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

67. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት አስተያየት አብዛኛው ሕንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑና መጠቀሚያ የተሰጣቸውም ቢሆን የሕንጻ አዋጁን ተግባራዊ ሳያደርጉ እንደሆነ ይህም ሌላ ሩቅ ሳንሄድ እንደ ምሳሌ የቀድሞ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከራየው ሕንጻ ራሱ የሕንጻ አዋጁን፣ ደንቡንና መመሪያውን ሳያሟላ የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዴት እንዳገኝ ለነሱም ጥያቄ የፈጠረባቸው መሆኑ፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መጠቀሚያ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የሚቆጣጠርበት የህግ ማዕቀፍ የሌለ በመሆኑ ይህን ለማሻሻል የሕንጻ አዋጁ ክለሳ እየተደረገበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

68. ሚ/ር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች አስፈላጊው እና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሕንጻዎች ደህንነታቸው አስጊ አለመሆኑን ሳይረጋገጥ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ መዋላቸው የህዝብ ደህንነትና ጤንነት ብሎም በሰው ህይወት ላይ ጉዳትና የህይወት ህልፈት እንዲፈጠር፣ ህንጻው ጤናማ እንዳይሆን የንብረት ውድመት በማስከተል የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሕንጻ ሹም ምደባን እና ውክልና በተመለከተ

69. የሕንጻ አዋጅ 624/2001ና የሌሎችን ሕጎች ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚያስችል አስፈላጊው የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያለው ሕንጻ ሹም በየከተሞቹ ሊመደብ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በሕንጻ አዋጁ 624/2001 ዓ.ም አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በሕንጻ አዋጅ 624/2001 አንቀፅ 57 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በአቅም ማነስ ምክንያት የሕንጻ ሹም ሊመድቡ ባልቻሉ ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ሹም በውክልና

አዋጁንና ሌሎች ህጎች ድንጋጌዎችን እንዲያስፈፅሙ መወከል ቢኖርባቸውም ድጋፍና ክትትል መደረግ ቢኖርበትም፤ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ባወጣው ዕቅድ እና በሕንጻ አዋጅ 624/2001 ዓ.ም አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በክልሎችና በከተሞች የሕንጻ ሹም መመደቡን እና በውክልና እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች

- በአዲስ አበባ ከባለስልጣን መ/ቤቱ እስከ ክፍለ ከተማው ባለው አደረጃጀት የህንጻ ሹም የሚል አደረጃጀት እስከ ሚያዝያ 01 2010 ዓ.ም ድረስ ያልነበረ መሆኑ፣
- በድሬዳዋ፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በጅማ፣ በለቀምት፣ የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በቡታጅራ፣ በሀዋሳ፣ በሸኖ፣ በፍኖተሰላም፣ በባህርዳር፣ በወልድያ፣ በላሊበላ፣ በመርሳ፣ በአላማጣ፣ በመቀሌ፣ በአሶሳ ከተሞችና በሀረሪ ክልል፣ ሶማሌ ክልል፣ በጋምቤላ ክልልና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የህንጻ አዋጁ ከወጣ ከ 4 ዓመት በኋላ ዘግይቶ የሕንጻ ሹም የተሾመ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን 5 ከተሞች፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን 7 ከተሞች፣ በማዕከላዊ ጎንደር 11 ከተሞች እና በደቡብ ወሎ ዞን 4 ከተሞች ሕንጻ ሹም ያልተሾመባቸው መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለመጠይቅ እና በቀን 5 ጥር 2009 ዓ.ም፣ በጥር 2010 ዓ.ም እና በሰኔ 2010 ዓ.ም የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ላይ ከተከለሱ ዶክመንቶች የተገለጸ መሆኑ፣

- በክልሎችና በከተሞች የሕንጻ አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል በሕንጻ አዋጁ መሰረት የሕንጻ ሹም ጽ/ቤት የሚል አደረጃጀት አለመኖሩ እንዲሁም
- በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በሦስቱ ከተማ ላይ የሌሎች ከተሞች የሕንጻ ሹም በውክልና አዋጁን እንዲያስፈጽም አለመደረጉ፣ በቀን16/06/2010 ዓ.ም በተሰጠ የክትትልና ድጋፍ ግብረ-መልስ እና የሰኔ 2010 ዓ.ም የተደረገ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ
- በቤንሻንጉል-ጉምዝ ብሔራዊ ክልል በአሶሳ ከተማ የህንጻ ሹሙ ጽ/ቤት ኃላፊ አዋጁ ካስቀመጠው የትምህርት ዝግጅት መስፈርት ያላሟላ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ከተማ የህንጻ ሹም ጽ/ቤት ኃላፊ አዋጁ ካስቀመጠው የትምህርት ዝግጅት መስፈርት ያላሟላ መሆኑ፣

- በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመቀሌ ከተማ ሕንጻ ሹም የትምህርት ዝግጅት በሌላቸው ባለሞያዎች ዲዛይኖች የሚጸድቅ መሆኑ፣
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በወልድያ ከተማ አስተዳደር በውክልና የተመደበው ሕንጻ ሹም የትምህርት ዝግጅቱ መደቡን የማያሟላ መሆኑ፣
- በአፋር ክልል በበጀት እጥረት ምክንያት አዋጁ በሚፈቅደው አደረጃጀት መሰረት የሕንጻ ሹም አለመደራጀቱ እና ስራው የሚሰራው ከመሬት አስተዳደር ጋር ተደርቦ የሚሰራ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች በሚገኙ ከተሞችና የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት መልስ፣ ከተከለሱ መረጃዎች እና በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው በከተሞች እና በክልሎች የሕንጻ ሹም አደረጃጀት ወጥ አለመሆኑ እና ችግሩን ለመፍታት ሚ/ር መ/ቤቱ በተለያየ መድረክ ከመወያየት ውጪ የተደረገ ነገር የሌለ መሆኑና ያለመቀበል ችግር እንዳለም በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ወቅት በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

73. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ሚ/ር መ/ቤቱ በአዋጁ አተገባበር የተለዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች በየክልሉ ላሉ ለሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ግብረ-መልስ እንደሚሰጥና በድጋፍና ክትትል ወቅት የሚለዩ ችግሮችን ከማመላከት ውጭ እርምጃ መውሰድ ስልጣንና ተግባር እንደሌላቸው መግለጻቸው፤ እንደዚሁም በድጋፍና ክትትል ወቅት የተለዩ አዋጆች አተገባበር ክፍተቶች ለክልሉ የበላይ ሃላፊዎች በግብረ መልስ እንዲያውቁት የገለጽንላቸው ሲሆን በቀጣይ ከየክልሎቹ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በመወያየት የሚስተካከል መሆኑ ገልጸዋል፡፡

74. ይሁን እንጂ

- በሕንጻ አዋጅ 624/2001 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1 እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል የዚህን አዋጅና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች

ለማስፈጸም የሚያስችል አስፈላጊው የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያለው ህንጻ ሹም ሊመደብ ስለሚገባ፣

- በሕንጻ አዋጁ 624/2001 ዓ.ም በአንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ 3 ማነስ ምክንያት የሕንጻ ሹም ሊመድቡ ባልቻሉ ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ሹም በውክልና አዋጁንና ሌሎች ህጎች ድንጋጌዎችን እንዲያስፈጽም ህንጻ ሹም መሾም እንዳለበት ስለሚገልፅ
- ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሕንጻ አዋጁ ተፈጻሚ (ተግባራዊ እንዲሆን) ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የሕንጻ ሹም አደረጃጀት እንዲፈጠር ማድረግ ስለነበረበት፣

የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

75. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎችና በከተሞች የህንፃ ሹም በሌለበት ከተማና ክፍለ ከተማ የሌላ ከተማ ህንፃ ሹም በውክልና አዋጁን እንዲያስፈጽም መደረጉን ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ አለማድረጋቸው፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጡ፣ ክትትሉና ቁጥጥሩ እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች ለሕብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት የጠበቀ ሕንጻ እንዳይገነባ ያደርጋል

## ሚ/ር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መከበራቸውንና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

76. ሚ/ር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መድረሳቸውን፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተልና ሊደግፍ ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ህጎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

77. ሚ/ር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ለክልሎችና ለከተሞች እንዲደርሱ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በክልሎችና በከተሞች የተላኩት ሕጎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውና ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ በአመት ሁለት ጊዜ ዕቅድ ቢያዝም በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሁለት ከተማ አስተዳደሮችና በሦስት ክልሎች በሚገኙ በሁሉም ከተሞች ድጋፍና ክትትል በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በአመት ሁለት ጊዜ ቢያቅድም በዕቅዱ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፣
- በ2008 በጀት አመት በዘጠኙም ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በመስክ ተገኝቶ በሕንጻ ግንባታና በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያለበትን ደረጃ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፣
- በ2009 በጀት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ቢሆንም ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ፤
- በ2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማና በሱማሌ ክልል አንድም ጊዜ በመስክ ተገኝቶ በሕንጻ ግንባታና በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያለበትን ደረጃ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፣
- በ2010 በጀት ዓመት በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመጀመርያው ግማሽ አመት ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ መሆኑና ነገር ግን ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. በናሙና በታዩት ከተሞችና ክልሎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን ክትትልና ድጋፍ ባለማድረጉ ምክንያት፡-
    - ✓ የህንጻ አዋጁ በሚያዘው መሰረትና አደረጃጀቱ በሚፈቅደው መሰረት የባለሞያ ስብጥር ያልተሟላ መሆኑ፣
    - ✓ በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የደህንነት አልባሳትን ተጠቅመው ግንባታውን እንዲያከናውኑ የግንዛቤ ማስጨባጫ ስራዎች ለስራ ተቋራጮች፤ ለአማካሪዎች፣ ለገንቢዎችና ለባለቤት የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የማይከናወን መሆኑ፣
    - ✓ ከክልሎች ክልሎች ከከተማ ከተማ የህንጻ አዋጁን ለማስፈጸም ያለው የሕንጻ ሹም አደረጃጀት ተመሳሳይ አለመሆን፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት በቃለ-መጠይቅ ወቅት ከተማ ላይ እንደማይወርዱ ምክንያቱም በክልል ላይ ሄደው የሚሰሩ መሆናቸውና የተወሰነ ከተማ በመምረጥ እንደሚያዩ እንደዚሁም 470 ከተማ ላይ እንውረድ ብንል እንደማይችሉ ይህም የበጀትና የአቅም የሌላቸው

መሆኑ፣ በ2008 ዓ.ም አዲስ ከመሆናችን አንጻር አላደረግንም በመሆኑም ያነሳችሁት ሃሳብ ተገቢ እንደሆነና ነገር ግን ጥልቀት ያለው ነገር እንደማያደርጉ ገልጸዋል፡፡

80. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ይህን ተግባር ለመፈጸም በስሩ የተደራጀ ቢሮ ያለ ሲሆን ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ በቢሮ እየተሰራበት ያለው ሁሉንም ክልሎችና የተመረጡ ከተሞች ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ሲሆን የህንጻ አዋጅ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች ላይ ሁሉንም ከተሞች ለማዳረስ የሰው ኃይልና የተሽከርካሪ እጥረት ያለባቸው መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

81. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም

- የሕንጻ አዋጅ 624/2001 ዓ.ም አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀፅ 3ና የሕንጻ መመሪያው ቁጥር 5/2003 ዓ.ም አንቀፅ 53 ንዑስ አንቀፅ 53.3 መሰረት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያው በክልሎችና በከተሞች ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል ስለሚል፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ በማቀድ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር ቢያደርግም ድጋፍ የሚደረግላቸው ከተሞችና ክልሎች ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2011 ዓ.ም አጋማሽ ዓመት ድረስ ከላይ የጠቀሱት ችግሮች ተመሳሳይ በመሆናቸው፣
- በሕንጻ ግንባታ፣ በመጠቀሚያ ፈቃድና በክትትል ቁጥጥር የሚሰራው ስራ አነስተኛ በመሆኑ (ከ2008 እስከ 2011 ዓ.ም ያሉት ችግሮች ተመሳሳይ መሆንና አለመስተካከላቸው)፣
- በሚሰጠው ግብረ-መልስ መሰረት ችግሮች ለመፈታት ከክልሎች ጋር አብሮ በመሆን እንዲስተካከል አለመደረጉ፣
- በእቅድ የተያዙት ተመሳሳይ ከተሞች የሚመረጥ መሆኑና የተመረጡትም ቢሆን ባለፈው የተሰጠው አስተያየት መሰረት መስተካከሉ ያልታየ በመሆኑ፣ እንዲሁም
- ይህን ለማስቀረት የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱን መከታተል ስለሚጠበቅበት፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ ሲያቅድ ያለውን ሃብት ታሳቢ አድርጎ እጥረት ካጋጠመውም እንዴት መፍታት እንዳለበት በእቅዱ አመላክቶ ወደ ተግባር መግባት ስለሚገባው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

82. የሕንጻ አዋጁን፣ ደንቡንና መመርያው በሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ ለመደረጋቸው ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ ፈጻሚና ሌሎች ባለድርሻ

አካላት ሃላፊነታቸውንና ሀገራዊ ግዴታቸውን እየተወጡ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እንዳይቻል፣ እነዚህ አካላት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በወቅቱና በአፋጣኝ እንዳይፈቱ ከማድረጉም በላይ በቅንጅት የሚሰሩትን ስራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜና ፍጥነት እንዳይሰሩ ያደርጋል፡፡ እየተገነቡ ያሉ ህንጻዎችም በሕዝብ ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

## የአቅም ግንባታ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ ተገቢውን አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል እቅም እንዲፈጠር መድረጉን በተመለከተ

83. ሚ/ር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ለክልሎችና ለከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ የወጡ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢውን አደረጃጀት፣ አሰራርና የሰው ኃይል እቅም እንዲፈጠር ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያደርግ፤ አፈጻጸሙን ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡ ከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ ክልሎች የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

84. ይሁን እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ እና ክልሎች የሕንጻ አዋጁና የተለያዩ የህግ መዕቀፎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀትና፣ አሰራርና የሰው ኃይል (ባለሙያ) እንዲሟላ አተገባበሩንና አፈጻጸሙን እንደማይከታተሉ ታውቋል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎችና ከተሞች፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በቡታጅራና በሀዋሳ፣ በፍኖተ ሰላምና በባህር ዳር ከተሞች ኤሌክትሮ መካኒካል ባለሞያ የሚል አደረጃጀት ባለመኖሩ ምክንያት ኤሌክትሮ መካኒካል ዲዛይን ዝም ብሎ (ሳይታይ) የሚጸድቅ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በሥሩ ባሉ በአስሩም ክፍለ ከተሞች፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በቡታጅራና በሀዋሳ፣ በፍኖተሰላምና በባህር ዳር ከተሞች እየተገነቡ ያሉ ሕንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ እደዚሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት ላይ ችግር መኖሩ መግለጻቸው፣
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሕንጻ ሹም ፅ/ቤት መዋቅሩ የሚፈቅደው 18 ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው 9 መሆኑ፣ አርክቴክቸራል ባለሞያ የሌለ መሆኑ፣

- በፍኖተ ሰላም መዋቅሩ የሚፈቅደው 11 ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ ያለው 7 ብቻ መሆኑ፣
- በአዳማ መዋቅሩ የሚፈቅደው 15 ሲሆን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 10 ብቻ መሆኑ፣
- በቢሾፍቱ መዋቅሩ የሚፈቅደው 50 ሲሆን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 42 ብቻ መሆኑ፣
- በቡታጅራ መዋቅሩ የሚፈቅደው 8 ሲሆን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 3 ብቻ መሆኑ፣
- በባሕር ዳር መዋቅሩ የሚፈቅደው 26 ሲሆን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 18 ብቻ መሆኑ፣
- የኦሮሚያ ክልል የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በጭሮና በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በቡታጅራ ከተማና በአማራ ክልል በፍኖተ ሰላም ከተማ ሚ/ር መ/ቤቱና ክልሎቹ የሰው ኃይልና አደረጃጀት በማሟላት ያደረጉት ክትትልና ድጋፍ የሌለ መሆኑን ከተሞቹ መግለጻቸው፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር በሚገኙ ከተሞች የተሟላ የሰው ኃይል የሌለ መሆኑ ለክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ መግለጻቸው፣

ታውቋል፡፡

86. በተጨማሪም፡-

- በሁሉም ክልሎች በ276 ከተሞች ላይ ተገቢው አደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም እንዲፈጠር ከማድረግ አኳያ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በየደረጃው ባለው አደረጃጀት ክትትልና ድጋፍ አድርጎ ወቅታዊ የጽሁፍ ግብረ-መልስ የመስጠት ክፍተት መኖር
- በኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ አደረጃጀቱ በሚፈቅደው (በመዋቅር በተፈቀደው) መሰርት የሰው ኃይል እንዲሟላ አለመደረጉ፣ በሰኔ 2010 ዓ.ም በተደረገ ድጋፍና ክትትል ላይ የተገለጸ መሆኑ
- በአፋር ክልል የሚገኙ ከተሞች (ዱብቲ፣ አባአላና አሳይታ) ላይ የሕንጻ ሹም አደረጃጀት እንዲኖር ያልተደረገ መሆኑ

- በጋምቤላ ክልል በሚገኙ ሦስት ከተሞች የሕንጻ ሹም አደረጃጀት እንዲፈጠር ያልተደረገ መሆኑ
- በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል በሚገኙ አምስት ከተሞች ላይ የሕንጻ ሹም አደረጃጀት እንዲኖር ያልተደረገ መሆኑ
- በሀድያ ዞን የአደረጃጀት ችግር መኖር ማለትም በሕንጻ አዋጁ መሰረት ለስራው የሚያስፈልጉ የባለሞያዎች ስብጥር የተሟላ አለመሆን በክትትልና ድጋፍ ሪፖርት በተደረገ በሰኔ 2010 ዓ.ም የተገለጸ መሆኑ
- ትግራይ ክልል በመቀሌና በአላማጣ ከተሞች የህንጻ አዋጁን በሚመለከት ስልጠና ለባለሞያዎች፣ ለአመራሩና ለህብረተሰቡ በሚፈለገው ደረጃ አለመሰጠቱ፣ ባብዛኛው የግንባታ ፈቃድ፣ ቁጥጥርና ክትትል እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጡ ሂደቱን ተከትለው የማይሰጡ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ከተማ የህንጻ ሹም አደረጃጀት ከተፈጠረ ጀምሮ ለከተማው ነዋሪ ለሌላ ሴክተር አመራሮች እና ለፅ/ቤቱ ሰራተኞች ከህንጻ አዋጅ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ያለመፈጠሩ
- አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባህርዳርና በወልድያ ከተሞች በፌደራል ደረጃ በኮዶችና ስታንዳርዶች ዙሪያ ስልጠና አለመሰጠቱ እንደሁም የሚደረገው የክትትልና ድጋፍ ስራው ወጥና መደበኛ አለመሆን፣
- በደብብ ክልል፣ በጅጅጋ ከተማ፣ አፋር ክልል እና ጋምቤላ ከተማ የሕንጻ አዋጁን ለሚያስፈጽሙ ባለሞያዎች በየደረጃው ላሉ አመራሮች የህንጻ አዋጁን በሚመለከት አስፈላጊው ስልጣና ግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ፣
- በሾኔ ከተማ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት የሰው ኃይል እጥረት መኖር (የአርክቴክቸራል፣ የሳኒተሪ እና የኤሌክትሪካል ባለሞያዎች የሌሉ መሆናቸው) በቀን 09/09/2009፣ 07/04/2010፣16/06/2010 እና 1/10/2010 በሚ/ር መ/ቤቱ በተደረገ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም በተሰጠ ግብረ-መልስ ላይ የተገለጸ መሆኑ

በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

87. በናሙና በታዩ ክልሎችና ከተሞች የስራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት በሰጡት ምላሽ፡-

- ክልሎች የሕንጻ ሹም የሚል ጽ/ቤት ቢኖርም የሕንጻ ሹም (እንደ አንድ የሥራ ሂደት) አደረጃጀት የሌለ መሆኑ ፡-

- በአዲስ አባባ ከተማ የአደረጃጀት ችግር ያለው መሆኑ ይህም የኤሌክትሮ መካኒካል ባለሞያ እስካሁን የሌለ መሆኑን፣
- የኦሮሚያ ክልል ኮንስትራክሽን ቢሮ በስሩ ለሚገኙ ከተሞች ስልጠና ያልሰጠ መሆኑ መግለጻቸው፣
- በኦሮሚያ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዳማ ከተማ በ2008 እስከ 2009 ዓ.ም ምንም ዓይነት ስልጠና ያልተሰጠ ሲሆን በ2010 ዓ.ም ስልጠና ቢሰጥም በቂ አለመሆኑ መግለጻቸው፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በጭሮና በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በቡታጅራና በፍኖተሰላም ከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ በኮድና እስታንዳርድና በአዋጁና በህግ ማቀፎቹ ላይ ምንም ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑ፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ ከተማ የኤሌክትሪካልና የሳኒተሪ ባለሞያ የሌለ መሆኑ እና መዋቅሩ የሚፈቅደው 7 ባለሞያ ሲሆን ነገር ግን አሁን ያለው የሰው ኃይል 5 ባለሞያ ብቻ መሆናቸው፣
- ከተሞች የሰው ኃይል፣ የበጀት እጥረት ስላላቸው
- እና አቅም ስለሌላቸው የግንባታ ፈቃድ ሲሰጡ ሂደቱን ተከትለው የማይሰጡ መሆኑ፣
- ከተሞች የሰው ኃይል፣ የበጀት እጥረትና አቅም በግንባታ ላይ ያሉ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የመጠቀሚያ ፈቃድ የማይሰጣቸው መሆኑ፣
- ለክልሎችና ከተሞች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያልተሰጠ መሆኑ
- በሕንጻ ግንባታ የሚሣተፉ ባለሞያዎች፣ ተቋራጮችና አማካሪዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎች ያልተሰራ መሆኑ መግለጻቸው፣
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑና በፖሊሲው፣ የህግ ማዕቀፎች፣ ኮድና ስታንዳርድ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጠና ያልሰጠ መሆኑና
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር መዋቅሩ በሚፈቅደው መሰረት የሰው ኃይል (የአርክቴክ ባለሞያና የኤሌክትሮ መካኒካል ባለሞያ) የሌለ መሆኑ ይህም በስራቸው ላይ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑ፣

- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱና በክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ በኮድና ስታንዳርድ ላይ ምንም አይነት ስልጠና እና ምንም አይነት የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጎላቸው የማያውቅ መሆኑ በመዋቅሩ መሰረት የሰው ኃይል የሌለ መሆኑ (ኤሌክትሪ ባለሞያና ኤሌክትሮ መካኒካል ባለሞያ)
- የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ በአዲሱ ኮድና ስታንዳርድ ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤ ስለሌለ (ስልጠና ስላልተሰጠ) የህንጻ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሀብቶች በድሮው ኮድና እና ስታንዳርድ እየሰሩ በመምጣታቸው በስራቸው ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑ፣
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በቡታጅራ የተለያዩ የህግ-ማዕቀሮች፣ ኮድና ስታንዳርዶች ላይ ሰልጣና ያልተሰጠ መሆኑ፣ ፖሊሲው ላይ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ የተለያዩ የህግ-ማዕቀፎች፣ ኮድና ስታንዳርዶች የማስተዋወቅ ስራ ያልሰራ መሆኑና የቴክኒክ ድጋፍ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- በከተሞች የኤሌክትሮ መካኒካል የሚሰሩ ባለሙያዎችና ሌሎች ወዘተ… የሌለ መሆኑ
- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፍኖተ ሰላም ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች፣ ኮዱና ስታንዳርዶች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፣ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣ ከህንጻ አዋጁ፣ ደንብና መመሪያ በተያያዘ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑ፣ ኮድና ስታንዳርዶች ላይ የቴክኒክ ስልጣና ያልተሰጠ መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ እንደተገለጸው ስልጠናዎች ከ2008 እስከ 2009 ዓ.ም በሚፈለገው መጠን የሰጡ መሆናቸው፤ ነገር ግን ሥልጠና የተሰጠው የሥራ ኃላፊ በየጊዜው ስለሚቀያየር መሆኑና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልሎች እና በከተሞች የሰው ኃይል እጥረት ያለ መሆኑና አደረጃጀቱ በተመለከተ ገና እየተሰራ መሆኑ፣ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ ትክክል መሆኑ የገለጹ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሰው ኃይል እጥረት እንዳለባቸውና ህጉ በሚፈልገው መሰረት እየተሰራ እንዳልሆነ እንደዚሁም አደረጃጀቱ እየተሰራ እንደሆነና ክልሎች ላይ ግን

ችግር መኖሩ፣ የህንጻ ሹሞች ተጠሪነታቸው ለከተማው እንዲሆን እየተሰራ እንደሆነ ሆኖም ግን ለእያንዳዱ ክልል ማስገደድ እንደማይችሉና ችግሩን አይተው ዝም እንዳላሉ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

89. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አሁን ባለው ሁኔታ ቢሮው ሁሉንም ክልሎችንና የተመረጡ ከተሞች ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ሲሆን ሁሉም ክልሎች ማለትም የሕንጻ አዋጁ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች ላይ ሁሉንም ከተሞች ለማዳረስ የተሸከርካሪ እጥርት ያለባቸው መሆኑ፣ ባለፉት አመታት ስራ ላይ የነበሩ የህንጻ ኮዶችና ስታንዳርዶችን የመከለስ፣ ተጨማሪ አዲስ በማዘጋጀት ለክልሎች፣ ለከተሞች፣ ለዩኒቨርስቲዎችና ለባለድርሻ አካላት በማከፋፈል በነዚሁ ኮዶችና ስታንዳርዶች ላይ ለሁሉም ክልሎችና ከተሞች ላሉ የምህንድስና ባለሞያዎች ስልጠና እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን ይህንን ሰነድ በተገቢው ስራ ላይ ስለመዋሉ ሚ/ር መ/ቤቱ በ2010 ዓ.ም ሁለት ጊዜ በ2011 ዓ.ም በመጀመርያው ሩብ ዓመት ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ ድጋፍና ክትትል ስራ ተከናውኖ ስለአፈጻጸሙ ለክልሎች ግብረ-መልስ የሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

90. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም፡-

- በ2011 ዓ.ም አንደኛ ሩብ ዓመት (የመጀመርያው ግማሽ አመት) ክትትልና ድጋፍ ተደርጎ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል የተባለው ኦዲቱ አስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፣
- በጭሮ፣ በቢሾፍቱ፣ በቡታጅራና በፍኖተሰላም ከተሞች ከ2008 እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎ ግብረ-መለስ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ከ2008 እከከ 2011 ዓ.ም ድረስ የአደረጃጀት፣ የሰው ኃይል እጥረት እና የግንዛቤ ችግር አሁንም ድረስ ያለ በመሆኑ እና
- በማቋቋሚያ አዋጅ 1097/2011 ዓ.ም እንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 1(ሸ)፣ በሕንጻ አዋጁ 624/2001 ዓ.ም ንዑስ አንቀፅ 4 እና የሕንጻ መመርያ 5/2003 ዓ.ም ንዑስ አንቀፅ 53.4 አግባብነት ካላቸው ፌደራል መንግሰት አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሁም የሰው ኃይል እንዲሟላና አቅም እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ ስለነበረበት

የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

91. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ለክልሎችና ለከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታ፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ ተገቢው

አደረጃጀትና አሠራርና የሰው ኃይል አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ ሥራዎችን የማይሰራ ከሆነ አዋጁን ለማስፈጸም በስትራቴጂክ ዕቅድና በያመቱ የሚያዙ ዕቅዶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ሲሆን የወጣው የህንጻ አዋጅና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ ክልሎች ለከተሞች ድጋፍና ክትትል በማድረግ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ የማያደርግ ከሆነ የሕንጻ አዋጁን እና የህግ ማዕቀፎች እንዲከበሩ የማያደርግ ሲሆን የሚገነቡ ሕንጻዎች ለህዝብ ጤንነትና ደህንነት እስጊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ ቁጥር ያላቸው ስለመሆኑ

92. በክልሎችና በከተሞች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያላዉ የተሰጠበትን ቀን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገልፅ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ ናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎችና ከተሞች፡-

- ✓ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጭሮ ከተማ ከተሰጡ 7 ህንጻዎች በአዳማ ከተማ 7 ህንጻዎችና በቢሾፍቱ ከተማ 9 ህንጻዎች የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር የሌለው እና የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የማይገልፅ መሆኑ፣
- ✓ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ 4 ህንጻዎች የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር የሌለው እና የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የማይገልፅ መሆኑ፣
- ✓ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በፍኖተ ሰላም ከተማ 15 ህንጻዎች የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር የሌለው እና የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የማይገልፅ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይህ ግኝት እኛም በመስክ ስራ ወቅት ያገኙት እንደሆነና መጠቀሚያ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የሚቆጣጠሩበት የህግ መዕቀፍ የሌለ በመሆኑ ይህን ላማሻሻል የሕንጻ አዋጁ ክለሳ እየተደረገበት እንደሆነ በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጻዋል፡፡

95. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የሕንጻ ደንብ 243/2003 አንቀፅ 8 የተደነገገ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ በህንጻ አዋጁ 624/2001 አንቀፅ 57 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በከተሞችና በክልሎች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ ኮድ ቁጥር ያለው፣ የተሰጠበትን እና አገልግሎት የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገልጽ መሆኑን ሥርዓት

ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ መከታተል እና ተግባራዊ መሆኑን መምራት ስለሚጠበቅበት እንዲሁም የተሰጠው ምላሽ ከግኝቱ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ምክንያቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

96. የሚሰጠው የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ ኮድ ቁጥር ያለው፣ የተሰጠበትን እና አገልግሎት የሚያበቃበትን ጊዜ የማይገለጽ ከሆነና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም በወጣው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን የማይከታተል ከሆነ ለህገወጥ አሰራር በር ሊከፍት እና ህገወጥ የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለማንኛውም የሕንጻ ምድብ ዓይነቶች የሚቀርቡ ዲዛኖች መዘጋጀት የተመዘገቡ ባለሞያዎች ስለመሆኑን

97. በክልሎችና በከተሞች ለማንኛውም የሕንጻ ለሚገኝበት ምድብ የሚጠየቁ የዲዛይን ዓይነቶች መዘጋጀት ለየሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ ባለሞያዎች መሆን አለበት፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በየአመቱ በእቅድ በመያዝ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮችና በሦስት ክልሎች በሚገኙ ከተሞች ፡-

- ✓ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 10 የግንባታ ፈቃድ የቀረቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ በየሕንጻ ምድቡ የሚቀርቡ ዲዛይኖች በኮንሰላልታንት የማይዘጋጀ መሆኑ፣
- ✓ የሕንጻ ምድብ የሕንጻውን ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመኖሩ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ
- ✓ በጭሮ ከተማ 6 የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣
- ✓ ለሁሉም የሕንጻ ምድቦች የሕንጻ ምድብ የሕንጻውን ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመኖሩ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ሚ/ር መ/ቤት ያደረገው ክትትል እና ድጋፍ የሌለ መሆኑ
- ✓ በአዳማ ከተማ 4 የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣
- ✓ በቢሾፍቱ ከተማ 2 የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣

- ✓ በፍኖተ ሰላም ከተማ 2 የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣
- ✓ በቡታጅራ ከተማ 1 የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣
- ✓ በሀዋሳ ከተማ በ2008 ከተሰጡ የግንባታ ፈቃድ የቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣
- ✓ የፍኖ ተሰላም የከተማ በተመዘገበ ባለሙያ የሚሰራ ቢሆንም አንዳንዴ ኮፒ የሚያመጡ ሰለሆነ ትክክለኛ ይሁን ለማወቅ አስቸጋር የሆነባቸው መሆኑ፣
- ✓ በፍኖተ ሰላም ከተማ 2 የግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ዲዛይኖች ለምድቡ የሚጠየይቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመን የተደሰ አለመሆኑ፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን 36 ባለሙያዎች መስፈርቱን ሳያሟሉ በዲዛይን ዝግጅት የተሳተፉ መሆናቸው፣ 31 ባለሙያዎች በንድፍ ወረቀት ውስጥ ቢኖሩም ዲዛይኑን ስለማዘጋጀታቸው በአማካሪው ድርጅት ውስጥ ስማቸው ያልተገኘ መሆኑ፣ 19 ባለሙያዎች የባለሙያ ፈቃድ ሳያድሱ በዲዛይን ስራ ላይ የተሳተፉ መሆናቸው፣ 9 አማካሪ ድርጅቶች የፎርጅድ ላይሰንስ ዲዛይን እንዲዘጋጅ ያደረጉ መሆናቸው፣ 4 ባለሙያዎች ያለ ንግድ ፈቃድ የፕራክቲሲንግ ላይሰንስ ብቻ በማያያዝ ሙሉ ዲይዛን በማስገባት ፈቃድ ያገኙ መሆናቸው፣ 2 በሳይት ላይ በተቆጣጣሪነት የተመደቡ ባለሙያዎች በመመርያው መሰረት መስፈርቱን ሳያሟሉ የሚሰሩ መሆናቸው፣ 8 የተቋራጭ ባለሙያዎች ያልታደሰ ፈቃድ በመያዝ ስራ ውስጥ መሆናቸው፣ 15 ፕሮጀክቶች ምንም ዓይነት የአፈር ምርመራ ሪፖርት ሳያቀርቡ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑ፣ 6 ባለሙያዎች የአፈር ምርመራ ሪፖርት ሲያቀርቡ ምንም አይነት ንግድ ፈቃድ እና የባለሙያ ላይሰንስ መረጃ የሌላቸው መሆኑና 39 ባለሙያዎች ምንም አይነት ንግድ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ኮንስትራክሽን ቢሮ በተደረገ ኮንስትራክሽ ኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- ✓ በባህርዳር ከተማና በመቀሌ ከተማ በበጀት እጥረት ምክንያት በሚል በውጭ ሀይል (Out Source) ተደርገው መፅደቅ የነበረባቸው ዲዛይኖች በማይመለከተው

ባለሞያ በውክልና እንዲጸድቁ መደረጉ ሚ/ር መ/ቤቱ በባህር ዳር መቀሌ እና ሰመራ ከተሞች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣

- ✓ በጋምቤላ የግንባታ ፈቃድ አግኝተው ለሚገነቡ ግንባታዎች እንደየህንጻው ምድብ ለግንባታው በሚመጥን በተመዘገቡ ስራ ተቋራጮች እንዲገነቡ ተገቢ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ በሚ/ር መ/ቤቱ በተደረገ ድጋፍና ክትትት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- ✓ በአፋር ክልል፣ በሱማሌ ክልልና የኦሮምያ ኮንስትራክሽን ቢሮ የግል ግንባታዎች በተመዘገቡ ስራ ተቋራጮች አለመሆኑ፤
- ✓ በላሊበላ፣ በወልድያ፣ መርሳና ቆቦ ከተሞች ባልታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ፕላኖች የሚጸድቁ መሆኑ በሰሚን ወሎ ዞን ከተማ ኮንስትራክሽን መምርያ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖረት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- ✓ በጅጅጋ ከተማ፣ በድሬዳዋ ከተማ፣ በሀረሪ የግንባታ ፈቃድ አግኝተው ለሚገነቡ ግንባታዎች እንደየ ሕንጻው ምድብ ለግንባታው በሚመጥን በተመዘገቡ ስራ ተቋራጮች እንዲገነቡ ተገቢ ክትትል የማደረግ መሆኑ የግል ግንባታዎች በተመዘገቡ ስራ ተቋራጮች አይሰሩም እንዲሁም ማን እንደሚገነባቸው አለመታወቁ በባህር ዳር መቀሌ እና ሰመራ ከተሞች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል ሪፖተት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- ✓ በሶማሌ ክልል ለየምድቡ የሚቀርቡ ዲዛይኖች ፈቃድ ባለውና በተመዘገበ የዲዛይን አማካሪ የማይዘጋጁ መሆናቸው፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ባልተመዘገቡና ፍቃዳቸውን ባላደሱ ባለሞያዎች፣ ኮንትራክተሮችና የሥራ ተቋራጮች ስለመሰራቱ መረጃው ስለሌለን ተሰጥቶን ለቀጣይ ክትትል እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

101. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ አለመከታተሉ እና ያላሳደሱትን ፈቃድ አለመሰረዙ በህገወጥ መልክ የሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮች እንዲኖሩ፣ ግንባታዎች ከአሰራር ውጪ እንዲሆኑ እየፈረሱ አደጋ የሚያደርሱ ሲሆን ለብክነትም ይዳርጋል፤ በክልል እና በከተሞች ያሉ የሚገነቡ ግንባታዎች በተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች መሆኑን ድጋፍ፣

ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ ከሆነ ሕንጻዎቹ ለሕዝብ ጤንነትና ደህንነት አስጊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

**በሕንጻ አዋጁ መሠረት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ መቋቋሙን በተመለከተ**

102. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል በሕንጻ አዋጁ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ቦርዱ መቋቋሙን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

103. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ ክልሎችና ከተሞች፡-

- በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች የሕንጻ አዋጁ ከወጣ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ በአዲስ አበባ በሚያዚያ 1 2010 እና በድሬዳዋ በየካቲት 6 2010 የይግባኝ ሰሚ ቦርድ እንዲቋቋም የተደረገ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚ ቦርድ አማካኝነት የተፈቱ ቅሬታዎች አለመኖራቸው፣
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡- የክልሉ ኮንስትራሽን ቢሮ፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፡- በቡታጅራ፣ በሀዋሳ ከተሞችና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡- በፍኖተ ሰላም ከተማና በባህር ዳር ከተሞች በህንጻ አዋጁ መሠረት በሕንጻ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደረገው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት መልስና በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. በተጨማሪም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በሻሻመኔ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት፡- በወልድያ፣ ቆቦ፣ መርሳ ከተሞች፣ በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሰት፡- በሆሳዕናና በሸኖ ከተሞች፣ በአፋር ክልል፡- ዱብቲ፣ አሳይታ፣ አባአላ፣ አዋሽና ሰመራሎግያ ከተሞች፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት፡- በመቀሌ ከተማና በአላማጣ ከተሞች፣ በሐረሪ ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በጋቤላ ክልል፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በህንጻ አዋጁ መሠረት በሕንጻ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

105. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል

ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በክልሎችና በከተሞች ያልተቋቋመ መሆኑና በቀጣይ ችግሩን ለመፍታት ጥረት እንደሚደረግ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

106. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው ክፍተቱ በእነሱም በኩል መታየቱንና ግብረ-መልስ የሰጡ መሆናቸውን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልጸዋል፡፡

107. በሕንጻ ግንባታ ፈቃድ፣ በክትትልና ቁጥጥር እና በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን (ቅሬታዎች) ለመፍታ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ እንዲቋቋም አለመደረጉ በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ በገለልተኝነት ውሳኔ እንዳያገኙ ከማዳረጉም በላይ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይቀረፉ አሉታዊ እገዛ ደርጋል፡፡

## በግንባታ ወቅት አስፈላጊው የደህንነት ጥንቃቄዎችን በማድረግ ግንባታዎች የሚከናወኑ መሆኑ በተመለከተ

108. ማንኛውም አሰሪ በግንባታ ወቅት የሥራ ቦታዎች በሠራተኞች ደህንነት እና ጤንነት እንዲሁም በሕብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

109. ይሁን እንጂ ናሙና በታዩ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች እና በሦስቱ ክልሎች ያሉ ከተሞች፡-

- በግንባታ ወቅት የደህንነት ጥንቃቄዎች በተመለከተ በሰው ላይና በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑና በአግባቡ በተደራጀ ሁኔታ የአደጋ መረጃዎች የማይያዙ መሆኑ፣
- በግንባታ ወቅት የሚስተዋሉ ግልጽ የድህንነት (safety standards) አለመሟላት እና በተደጋጋሚ አለመከበር፣
- ሰራተኞች ሄልሜት፣ የደህንነት ጫማ፣ የደህንነት መጠበቂያ አልባሳትንና የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ የማይሰሩ መሆናቸው በሰውና በንብረት ላይ አደጋ የሚደርስ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡- በ40/60 ኮንዶሚንየም (ልዩስሙ ቦሌ በሻሌ ቃጢላ ኮንዶሚንየም)፣ ልዩ ስሙ ቦሌ ሃያት 49 ማዞርያ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ቦሌ አራብሳ፣ 40/60 ኮንዶሚኒየም ልዩ ስሙ በቦሌ ክፍለ ከተማ

ወረዳ 10 49 ማዞርያ፣ 22 ዳውን ታውን ቦሌ ክፍለ ከተማ እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ 4 ኪሎ አካባቢ (እሪ በከንቱ ሰፈር) በግንባታ ወቅት የሞትና የአካል ጉዳት የደረሰ መሆኑ ታውቋል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ አራት ተያይዟል፡፡**

110. በተጨማሪም፡-

- በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ፣ በጅማ፣ በለቀምትና በመቱ ከተሞች፣ በአማራ ክልል በወልድያ ከተማ፣ በአፋር ክልል፣ ሀረሪ ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልና በትግራይ ክልሎች በግንባታ ወቅት የደህንነት ጥንቃቄዎች በተመለከተ በህንጻ መመሪያው መሠረት የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች የማይሰሩ መሆኑ፣
- በግንባታ ወቅት የሠራተኞችን ደህንነት መጠበቂያ አልባሳትና መሳሪያ ሳያሟሉ ሥራዎችን የሚሰሩ መሆኑ፣ በዚህም የተለያየ የንብረት የአካል ጉዳትና የህይወት መጥፋት እየደረሰ መሆኑ፣
- የሕንጻ ግንባታው ሲሰራ የአፈር መንሸራተት መከላከያ የማይደረግ መሆኑ

በኦዲት ወቅት በተደረገው ቃለ-መጠይቅ፣ የመስክ ምልከታና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

111. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና አስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊዎች እና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ሀሳቡን እንደሚቀበሉት ገልጸዋል፡፡

112. በኮንስትራክሽን ሥራ አካባቢ በሰዎች ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ የማይጥሉ የመሳሪያዎች እንቅስቃሴና ሥራ አካባቢ በመጠቀም ግንባታዎች ካልተከናወኑ የግንባታ ሠራተኞች ድህንነት በዘላቂነት እንዳይጠበቅ በማድረግ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ህይወት ለሞትና ሌሎች የአካል ጉዳቶች ሠለባ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## ሚ/ር መ/ቤቱ በሕንጻ ግንባታና መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ጥናት ማድረጉን በተመለከተ፣

113. ሚ/ር መ/ቤቱ በህንጻ ግንባታና መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት ሊያዘጋጅና ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

114. ይሁን እንጂ ሚኒስትር መ/ቤቱ የግንባታ ፈቃድ፣ መጠቀሚያ ፈቃድ፣ ክትትልና ቁጥጥር ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ያልሆኑ እናሕገወጥ የሕንጻ ግንባታ ላይ ያሉ

ችግሮችን በመለየት እና ቅደም ተከተል በመስጠት በዚሁ መሰረት ወደ ትግበራ ለመግባት የሚያስችል ጥናት ያላከናወነ መሆኑን ታውቋል፡፡

115. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደ ናሙና አዲስ አበባን በዕቅድ በመያዝ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ አግኝተው አገልግሎት ላይ የዋሉትን ህንጻዎች ለአረጋዊያንና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለመለየት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ነገር ግን በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት የሌሎች ክልሎችና ከተሞች ያልሰሩ መሆናቸውን እና ሀሳቡን እንደሚቀበሉት በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

116. በሕንጻ ግንባታ አሰጣጥ፣ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር፣ በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ በሕገወጥ ግንባታ፣ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን እና አለመሆናቸውን ያሉ ችግሮችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት አለመጠናቱ በክልሎች፣ በከተሞችና በፈጻሚ አካላት እያጋጠማቸው ያሉ ዝርዝር ችግሮች እንዳይታወቁና በፍጥነት ችግራቸው እንዳይፈታ ያደርጋል፡፡

## በሕንፃ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

### ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን የተዘጋጀላቸው መሆኑን በተመለከተ

117. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሊለዩና መስፈርቱን ማሟላት አለማሟላታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ መስፈርቱን ያላሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

118. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ

ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ተግባራዊነቱን እንደማይከታተል ታውቋል፡፡

119. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና አስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት የሌለ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ ገልጸዋል፡፡

120. ሰለጉዳዩ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡

121. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊውን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ተለይተው የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር አለመደረጉ ተገልጋዮች በሕንጻ አዋጁ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ ሕብረተሰቡን ከአደጋ እና ደህንነት መጠበቅ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## ግንባታቸው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዘርፍ ወደ ሌላ ዘርፍ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ዲዛይን ብቁ መሆናቸውን መረጋገጡን በተመለከተ

122. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንባታቸው ከታለመላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ሥርዓቱ በከተሞች ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

123. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንባታቸው ከታለመላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

124. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና አስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል

ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሲመልሱ ግንባታቸው ከታለመላቸው ውጪ ለመቀየር ሲፈለግ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ላይ ገልጸዋል፡፡

125. ስለጉዳዩ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡

126. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንባታቸው ከታለመላቸው ውጪ ለመቀየር ሲፈለግ ከዲዛን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለተቀየረው ዘርፍ ህንጻዎቹ ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ተገቢውን አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## ከሕንጻ አዋጁ ጋር በተያያዘ ለሚ/ር መ/ቤቱ በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በተሰጡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ

127. ከሕንጻ አዋጁ ጋር በተያያዘ ለሚ/ር መ/ቤቱ በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በሚሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ሊወሰድ ይገባል፡፡

128. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በጥር 2004 ዓ.ም በተደረገው የሕንጻና የመኖርያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥርን በተመለከተ በተደረገ ክዋኔ ኦዲት ላይ፡-

- በክልልና ከተማ አስተዳደር በጀትና ድጋፍ ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት አለመደረጉ፣
- ያለአማካሪ መሀንዲስ ክትትልና ቁጥጥር የሚሰሩ የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎች የሚሰሩ መሆናቸው፣
- የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ቦታ የግንባታ መከታተያ የመረጃ መዝገብ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የግንባታ ተቆጣጣሪዎች ክትትል በሚያደርግበት ወቅት ያገኙትን መረጃ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ የማያሰፍሩ መሆኑ፣
- በግንባታ ሂደት ለግንባታ ግብዓት የሚውሉ የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ የማይደረግ መሆኑ፣

- የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ግንባታ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ (ተደራሽ) ያደረጉ አለመሆናቸው፣ ይህም በባህር ዳር ከተማ 20 ሰው የሞተ መሆኑ እና በ36 ሰው ከባድ የአካል ጉዳት እንዲሁም በተቀሩት ላይ ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰ መሆኑ፣ ሴት ባክ (የወሰን ርቀት) ሳይጠብቁ መስራት፣
- የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸው ህንፃዎች መስታወቱ ደረጃውን የጠበቀና ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በቅድምያ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- መሪ ሰነድች አስገዳጅ ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩና የሚተገበሩ አለመሆናቸው
- በግንባታ ሥራ ሊይ የተሠማሩ ሠራተኞች የደህንነት መጠበቂያዎችን የሚጠቀሙ አለመሆኑ፣
- በምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ሲገነቡ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያና የማምለጫ አመላካቾች የማይዘጋጁ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት የታወቀ ሲሆን ሆኖም ግን በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እስከ አሁን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

129. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመጋቢት 2009 ዓ.ም ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ላይ፡-

- የሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና እድሳትን በተመለከተ
- ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ፣
- ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ማሳደሳቸውን በተመለከተ፣
- ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በተመለከተ
- ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ
- ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት በሚውሉ ግንባታዎች ላይ የሚደረግ የክዋኔ ኦዲትን ያልተሰራ መሆኑ፣

በኦዲት ሪፖርት በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እስካሁን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰዱ መሆኑ፣

- በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመጋቢት 2009 ዓ.ም ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል በተመለከተ የተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ለአካል ጉዳተኞች በሚገነቡ ሕንፃዎች እና ለህዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ የተከናወነ

የክዋኔ ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እስካሁን ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰዱ መሆኑ፣

- በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኮንሰትራክሽን ኦዲት ዳይሬክቶሬት በሚያዝያ 24/2010 ዓ.ም የ2009ና 2010 ዓ.ም ዲዛይን የጸደቀላቸውና የሕንጻ ፕሮጀክት ዲዛን እና ተያያዥ ሰነዶች አጻጻደቅ ሂደት በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት በተደረገ የኮንስትራክሽን ኦዲት
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚጸድቁ የኤልክትሪካል ዲዛይን ሪፖርት የሚገልጹት ዲዛይኑን ሳይሆን የዲዛይን አሰራር ሂደት (Design Steps) ብቻ የሚያሳዩ መሆናቸው፣
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚጸድቁ የህንጻ ዲዛይኖች የኤሌክትሪካ ሪፖርቶች ለተለያዩ የሕንጻ ፕሮጀክቶች ተመሳሳይና ኮፒ መሆናቸው፣
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቁ የህንጻ ዲዛይኖች እንድ አርክቴክቸራል ዲዛይን (የሥነ-ህንጻ) ሲጸድቅ ማካተት ያለበት የመዳረሻ መንገድ ስያሜ፣ ወደ ህንጻው መግብያ አመላካች ምልክት፣ የተፈጥሮው የመሬት ተዳፋት ፕላን (Contour plan)፣ ከዋናው ፋሳሽ ቆሻሻ መስመር ጋር የሚገናኝ ከሆነ የማስወገጃ መስመር ያለበት ቦታ ርቀት፣ የጣርያ የተፋሰስ አቅጣጫ የተዳፋትነት መጠን እና የመሳሰሉትን ያላካተተ መሆኑ
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቁ የሕንጻ ዲዛይኖች ግንባታው የሚሰራበትን አካባቢ የሚያሳዩ፣ በእስኬል ያልተሰሩ እና በግልፅ የሚታዩና በቂ መረጃ መስጠት የማይችሉ መሆናቸው፣
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ የጸደቁ የህንጻ ዲዛይን ሪፖርቶች ፍዘታዊ ስሌት (Statical Calculation) የግንባታው ዲዛይን አጠቃላይ መነሻ (Fundamental Requirement) እና ታሳቢዎችን (Action to be Considered) የሚዘረዝር መግቢያ የሌለው እና ለዲዛይን የተጠቀሙበት ኮድና ስታንዳርድ የማይጠቅሱ መሆናቸው፣
    - በባለስልጣን መ/ቤቱ እስከ አሁን ባለው አሰራር የመካኒካል ዲዛይን በህንጻው መመሪያ መሰረት የማይጸድቅ መሆኑ፣
    - የአፈር ምርመራ ሪፖርት ውስጥ የመሸከም አቅም ውጤት ጋር አነጻጽረው ለግንባታው የሚሆን የመሰረት ዲዛይን ዓይነት እንዲሁም አዋጭ እና

ኢኮኖሚያዊ የሆነውን የመሰረት ዓይነት ያላቀረቡ መሆናቸው እና በአብዛኛው በቀረቡ የሪፖርት ጥራዞች ውስጥ መኖር የነበረባቸው ዋና ሰነዶች (Original Document) የሌሉ እና ቅጂ (Copy) ተደርገው የገቡ ሰነዶች መሆናቸው፣

- በተመለከተ የተሰራው የኮንስትራክሽን ኦዲት ላይ በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እስካሁን ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰዱ መሆኑ፣

- በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በውስጥ ኦዲተር በየካቲት 2010 ዓ.ም የሕንጻ ኪራይ ልዩ ኦዲት ሪፖርትን በተመለከተ በተደረገ ኦዲት ላይ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌለው መሆኑ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ በየወለሉ የሌለው መሆኑ፣ አጠቃቀሙን በተመለከተ ያልተለጠፈ መሆኑ፣ ሁለት ቤዝመንት እያለው አራት ተብሎ መከራየቱ፣ የመሰብሰብያ አዳራሽ አለው ተብሎ ነገር ግን የህንጻው ጣርያ ላይ በማዘጋጀት የተሰራ መሆኑን …ወዘተ በተመለከተ የተሰራው የክዋኔ ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት እስካሁን ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰዱ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሰ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

130. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሕንጻ አዋጁና ከሕግ ማእቀፎቹ ጋር በተያያዘ በተለያዩ አካላት በሚሰጡት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ከሕንጻ ግንባታ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ የአሰራር ስህተቶችን ወይም ድክመቶች እንዳያርም ከማድረጉ በተጨማሪ ተጠያቂነት ያለበት አሰራር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

## ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

133. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ የአሰራር

ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የሌለ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ኦንላይን ሲስተም የተጀመረ ቢሆንም ነገር ግን አሰራሩ ችግር ስለነበረው መቋረጡ፣
- በናሙና በታዩ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች እና በሦስቱም ክልሎች የግንባታ ፈቃድ፣ የክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ ማስረጃዎች በመሬት ልማት አስተዳደር ሥር በመሆኑ በኦዲት ወቅት ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም ከተወሰኑ ዶክመንቶች በስተቀር መረጃዎቹን በቀላሉ ሊያገኙ ባለመቻላቸው አለማቅረባቸው፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2008 ዓ.ም፣ የ2009 ዓ.ም ማስረጃ (የግንባታ ፈቃድ፣ የክትትልና ቁጥጥር እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሰነዶች) ተጠይቀው ሊያቀርቡ ያለመቻላቸው እና የ2010 ዓ.ም ማስረጃዎችም ግማሽ ያህሉ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
- በድሬዳዋ፣ በአዳማ፣ በቢሾፍቱ፣ በቡታጅራ፣ በሐዋሳ፣ በፍኖተ ሰላም እና በባህር ዳር ከተሞች የ2008፣ 2009 እና 2010 ዓ.ም ማስረጃዎች (የግንባታ ፈቃድ፣ የክትትልና ቁጥጥር እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ሰነዶች) ተሟልቶ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
- በሀረር ክልል፣ አፋር ክልል፣ ሶማሌ ክልል፣ ጋቤላ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልና በትግራይ ክልል በመቀሌና በአላማጣ ከተሞች ተመሳሳይ ሁኔታዎች መኖራቸው በ ሰኔ 2010 ዓ.ም የመስክ ስራ ሪፖርት ላይ የተገለጸ መሆኑ፣
- የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ ከቀረበ ቃለ-መጠየቅ ዘመናዊ መረጃ አያያዝ ስርዓት የሌለ መሆኑ ይህም በስራቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እየገጠማቸው መሆኑ መግለጻቸው፣
- ከማዕከል እስከ ክልልና ከተማ አስተዳደሮች ባለው አደረጃጀት የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ጠንካራ ያለመሆን፣
- በከተሞች ያሉ ማዘጋጃ ቤቶች፤ ከመሬት ልማት ማኔጅመንት እና ከኮንስትራክሽን ቢሮ ጋር ያለው መረጃ አያያዝና ልውውጥ ላይ ክፍተት ያለው መሆኑ ፣

- የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ ጠንካራ አለመሆን እና መረጃዎች በየደረጃውና በወቅቱ አለማግኘት ችግር መኖር፣
- ከማዕከል እስከ ክልልና ከተማ አስተዳደሮች ባለው አደረጃጀት የመረጃ ልውውጥ ስርዓታችን በሚፈለገው ደረጃ ጠንካራ ያለመሆን፣ በ2008 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ በ2010 ዓ.ም የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተሰጠ ግብረመልስ እና በ2011 ዓ.ም ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተገለጸመሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የባለስልጣን መ/ቤቱ ሰነዶች የግንባታ ፈቃድ፣ የክትትልና ቁጥጥር እንደዚሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ ፋይሎች በሚገባ እና በተደራጀ መልኩ ተደራጅተው የማይገኙ መሆኑ፣



መረጃ አያያዝ ችግር በአዲስ አበባ ከተማ የመሰረተ ልማትና ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለሥልጣን

134. ስለሁኔታው የየክልሎቹ ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊዎች እና የየከተሞቹ ሕንጻ ሹም ኃላፊዎች ማስረጃዎች ከመሬት ልማት ማኔጅመንት ጋር ያለ በመሆኑ በመረጃ አያያዝ ላይ ክፍተት እንዲኖር ማድረጉ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት ገልጸዋል፡፡

135. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች እና የኮንስትራክሽን ህግጋት ዝግጅትና አፈጻጸም ክትትል ቢሮ እና የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮዶችና አስታንዳርዶች ዝግጅትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው ከሚ/ር መ/ቤት እስከ ማዕከል (ክልልና ከተሞች) ጨምሮ መረጃ አያያዝ ችግር ያለበት መሆኑ፣ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በተለይም የካሪስ የሙከራ ትግበራ ላይ ሲሆን በሌላ በኩል አመታዊ ስታቲካል መፅሔት በ2010 ዓ.ም በማዘጋጀት በ2011 ዓ.ም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ስራ የተሰራ መሆኑ፣ በሌላ በኩል የሚኒስቴር መቤቱ የመረጃ ዳይሬክቶሬት የተሰባሰቡ መረጃዎች ዌይብ ፖርት ላይ እንዲጫኑ የማድረግ ስራ እየተሰራ በመሆኑና በቀጣይ የመረጃ ፕላት ፎርም በመዘርጋት ለመስራት በዕቅድ

ላይ መሆናቸውን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ እና በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

136. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውጤታማ የሆነ ቅንጅታዊ ሥራ እንዲኖረው መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ወጥ የሆነ አሰራር ሥርዓት ካልተዘረጋና የተጠያቂነት ሥርዓቱን ለማስፈጸም ሥራዎች ካልተሰሩ የመረጃ አቅርቦት ስርዓቱ የተበታተነ እንዲሆን፣ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጠው መረጃ ተዓማኒነት የሌለው እና መረጃዎች በቀላሉ እንዳይገኝ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደምያ

137. የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር (የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር) የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ዝውውሩና ቁጥጥሩን ለማካሄድ የሚስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች ሙሉ ለሙሉ (ባጠቃላይ) በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይናቸው እንዲጸድቅ የማይደረግ መሆኑና ግንባታቸው ከተገነባና እየተገነባ እያለ ዲዛይን የሚጸድቅ መሆኑና የመንግስት ግንባታዎች እንደማንኛውም ግንባታ በህንጻ አዋጁ መሰረት የመንግሰት ሕንጻ ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው፣ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግላቸው እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ የሚገነቡ ሕንጻዎች የግንባታ ፈቃድ አግኝተው እንዲገነቡ በተያዘው ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞች የሚካሄዱ ግንባታዎች የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ያገኘ ስለመሆኑ ሥርዓት ዘርግቶ ያልተከታተለ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከተሞች የሚዘጋጁ የዲዛይን ጥናቶችና ሕንጻ ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኛ፣ ለአረጋውያን የሚመቹ መሆኑን ሥርዓት ዘርግቶ ያልተከታተለ መሆኑ፣
- በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች በክትትልና ቁጥጥር ሂደት እንዲያልፉ ሚኒስትር መ/ቤቱ ሥርዓት በመዘርጋት ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ሂደትን ተከትለው እየሰሩ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣

- የሕንጻ አዋጅ 624/2001 የሌሎችን ሕጎች ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚያስችል አስፈላጊው የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያለው ሕንጻ ሹም በአንዳንድ ከተሞች ያልተሾመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአቅም ማነስ ምክንያት የሕንጻ ሹም ሊመድቡ ባልቻሉ ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ሹም በውክልና ሥራዎችን እንዲሰራ ስለመደረጉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መከበራቸውንና ተግባራዊ ስለመደረጋቸው የተደረገው ክትትልና ድጋፍ በዕቅዱ መሰረት ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ክልሎች የሕንጻ አዋጁና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀትና፣ አሰራርና የሰው ኃይል እንዲፈጠር አተገባበሩንና አፈጻጸሙን እየተከታተሉ ድጋፍ ባለማድረጋቸው ከተሞች በስራቸው ላይ ችግር እንደፈጠረባቸው የገለጹ መሆኑ፣
- በከተሞች የተሰጡ የግንባታ ፈቃድ ሰነዶች ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያልተሰጣቸው፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን ቀን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ ያልተገለጸ መሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልሎች በኩል ክትትል ተደርጎ ግብረመልስ ስለመሰጠቱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች በተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች መሆኑን ሚኒስትር መ/ቤቱና ክልሎች የሚከታተሉበት ሥርዓት ዘርግተው ክትትልና ቁጥጥር ያላደረጉ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል በሕንጻ አዋጁ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የይግባኝ ሰሚ ቦርድ መቋቋሙን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መቤቱ በግንባታ ሥራ አካባቢ የሰዎችን ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ላይ የማይጥሉ የመሳሪያዎች እንቅስቃሴና የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር አስገዳጅ የስራ ላይ ደህንነት ማረጋገጫ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህንጻ ግንባታና መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ ያሉ ችግሮችን ለይቶ ለመለየት የሚያስችል ጥናት በማድረግ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያላዘጋጀ መሆኑ፣

- ቀደም ሲል የተገነቡ ህንጻዎች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ያልተከታተለ መሆኑ፣
- ግንባታቸው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ጥያቄ ሲቀርብ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆኑን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተከታተለ መሆኑ፣
- ከሕንጻ አዋጁ ጋር በተያያዘ ለሚ/ር መ/ቤቱ በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በሚሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ያልወሰደ መሆኑ፣
- ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ያልተከታተለ መሆኑ፣

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

138. የቀድሞው የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር (የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር) የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ እና አዋጆች ደንቦች እና መመሪያዎች ለማስፈጸም የሚረዱ  እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለሚሰሯቸው ስራዎች የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- የሕብረተሰቡ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች እንደሌሎቹ ሕንጻዎች በሕንጻ አዋጁ መሰረት የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ፣ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ በመውሰድ ወደ አገልግሎት እንዲገነቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ሥራዎች እንዲሰሩ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ሂደቱን ተከትለው በተሟላ መንገድ እንዲተገበር መደረጉን ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የግንባታ ፈቃድ ሳይወስዱ ግንባታ ለሚጀምሩ የተጠያቂነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻዎች የከተማውን መሪ ፕላን መሰረት በማድረግ የፕላን ስምምነት አግኝተው መገንባታቸውን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ሚኒስተር መ/ቤቱ እየተከታተለ ግብረ-መልስ ሊሰጥና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚዘጋጁ የዲዛይኖች ጥናቶችና ግንባታዎች ለአካል ጉዳተኞች በሕዝብ መገልገያ ተቋማትና ተደራሽ እንዲሆኑ አስገዳጅ የዲዛን ስታንዳርድ በመተግበርና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ዲዛይን (Accessible Design) እንዲሁም ሁሉን አቀፍ ዲዛይን  (Universal Design) በማጣመር ተግባራዊ

እንዲሆን የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መደረጉን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል በማድረግ ድጋፍና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የሕንጻ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሂደትን ተከትለው በተሟላ መንገድ እንዲተገበር እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ለተገነቡ እና ለሚገነቡ ሕንጻዎች የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲጠናከር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድ በመያዝ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ተከትሎ በተሟላ መንገድ እንዲተገበር እንዲሁም የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግባቸው ሙሉ ለሙሉ እና በከፊል ለተጠናቀቁ ሕጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ለሚሰጡ ግንባታዎች የተጠያቂ የሚሆኑበትን የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ሚኒስተር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመሆን ክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች ለሕብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ተደራሽ እንዲሆኑና ጤንነቱን የጠበቀ ሕንጻ እንዲገነባ የሕንጻ ሹም ባልቋቋመባቸው ከተሞች የህንጻ ሹም እንዲኖር መደረጉን ሚኒስተር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሕንጻ አዋጁ 624/2001 ዓ.ም መሰረት የሕንጻ ሹም በሌለበት ሕንጻ ሹም በውክልና አዋጁን እንዲያስፈፅም መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ያሉ የሕንጻ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም ወደፊት የሚወጡ ሕጎች ተግባራዊነታቸውን ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሕንጻ አዋጁና የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢው አደረጃጀት፣ አሰራርና የሰው ኃይል እንዲፈጠር ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ክልሎች አተገባበሩንና አፈጻጸሙን እየተከታተሉ ድጋፍ በማድረግ ማስፈጸም የሚችል አደረጃጀትና የሰው ኃይል እንዲሟላ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- በከተሞች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ ሰነዶች አስቀድሞ የታተመ ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያላቸው፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን ቀን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ


የሚገልጽ መሆኑን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

- በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች በተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች የሚከታተሉበት ሥርዓት ዘርግተው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- በግንባታ ፈቃድ፣ በግንባታ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን (ቅሬታዎች) ለመፍታት እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በሌላቸው ከተሞች ቦርድ የተቋቋመ እና የቀረቡ ቅሬታዎች እየተፈቱ መሆኑን ሊያረጋግጥና ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መቤቱ የሕንጻ አዋጁ የደህንነት ደረጃዎችን ሳይጠብቁ የዲዛይን ወይም አማካሪ መህንዲስነት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሞያዎች ተጠያቂ የሚሆኑበትን አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ፣ በግንባታ ሥራ አካባቢ የሰዎችን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የማይጥሉ የመሳሪያዎች እንቅስቃሴና የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የግንባታ አካባቢ ስራተኞች ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በተግባር ላይ እንዲውል መደረጉን በማረጋገጥ ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡
- ሚኒስተር መ/ቤቱ በሕንጻ ግንባታ አሰጣጥ፣ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር፣ በመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ሕገወጥ ግንባታ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ እና ችግሮችን ለይቶ ጥናት በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በተግባር ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ሚኒስተር መ/ቤቱ ግንባታቸው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጭና በውስጥ ኦዲተሮች፣ እንዲሁም በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች እና ግብረ መልሶች በተሰጠው አስተያየት መሰረት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የድርጊት መርሃ ግብር (Action Plan) በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት የኮንስትራክሽን ዘርፍ መረጃዎችን በማሰባሰብና በዘመናዊ ሁኔታ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚደረግበት አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና የመሰረተ ልማት ቅንጅት ሕንጻ ሹም ጽ/ቤተና ዳይሬክትር፣ የከተማው ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሕንጻ ሹም ጽ/ቤት፣ የከተማው ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ የጭሮ፣ አዳማና የቢሾፍቱ የሕንጻ ሹም ኃላፊና የኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የቡታጅራ የኮንስትራክሽን ቢሮና የሕንጻ ሹም የስራ ሂደት፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍኖተ ሰላም ሕንጻ ሹም ጽ/ቤትና የከተማው ኮንስትራክሽን ቢሮ፣ የባህርዳር የህንጻ ሹም ጽ/ቤት ኃላፊ እና የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ እንዲሁም የቀድሞው ኮንስትራክሽን የሚኒስቴር መ/ቤት ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1 የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ ሁለት፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

የኦዲት አካባቢ፡- <u>የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን (“የምድብ ‘ሐ’ ሕንፃ”) በተመለከተ</u>

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| የሕንጻ ግንባታዎችና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ የሬጉላቶሪ ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ | 1. ሚ/ር መ/ቤቱ ለየሕንጻ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ መደረጉን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2. የሕንጻ አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎችና መመዘኛዎችን ክልሎች አውጥተው በስራቸው ለሚገኙ ከተሞች እንዲደርስና ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 3. ሚ/ር መ/ቤቱና ክልሎች በአቅም ማነስ ምክንያት የሕንጻ ሹም ሊመድቡ ባልቻሉ ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ሹም በውክልና አዋጁንና ሌሎች ህጎች ድንጋጌዎችን እንዲያስፈፅሙ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 4. ሚ/ር መ/ቤቱ አዋጁን ለማስፈጸም የተለያዩ የህግ-ማዕቀፎች፣ ኮድና ስታንዳርድ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 5. ሚ/ር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች በክልሎችና በከተሞች መከበራቸውንና ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 6. ሚ/ር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራባቸውን ልዩ ልዩ ኮዶች ሊያዘጋጅና ተግባራዊ መደረጉን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ሚ/ር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ለክልሎችና ለከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 8. በሚ/ር መ/ቤቱ የወጡ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተገቢውን አደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር እንዲዘረጋ ሊያደርግ፤ አፈጻጸሙን ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 9. ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞችና በክልሎች የሚገነቡ ሕንጻዎች የሕንጻ ግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትለው መሰራታቸውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. በክልሎችና በከተሞች ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛው ሰው የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ |

| | |
|---|---|
| | አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ያገኘ ስለመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11.በክልሎችና በከተሞች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያለው የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገልፅ መሆን ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የይገባል፡፡ |
| | 12.በክልሎችና በከተሞች ለማንኝውም የሕንጻ ምድብ ዓይነቶች የሚጠየቁ (የሚቀርቡ) ዲዛኖች መዘጋጀት የሚኖርባቸው ለሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ ባለሞያዎች መሆናቸውን የሚቆጣጠርበትን ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 13.በክልሎችና በከተሞች የሚዘጋጀው ዲዛይን (ፕላን) ከመፈቀዱ በፊት አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14.ሚ/ር መ/ቤቱ በክልሎችና በከተሞች የሚገነቡ ሕንጻዎች አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎላቸው የተገነቡ መሆኑን ሊከታተልና ሊደግፍ ይገባል፡፡ |
| | 15.ሚ/ር መ/ቤቱ በከተሞችና በክልሎች በ"ምድብ 'ሐ' ሕንጻ" ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሂደት ተከትለው እየተሰጣቸው መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 16.ከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ ክልሎች የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ |
| | 17.ሚ/ር መ/ቤቱ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል በሕንጻ አዋጁ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የይግባኝ ሰሚ ቦርድ መቋቋሙን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 18.አዋጅ 624/2001ና የሌሎችን ሕጎች ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚያስችል አስፈላጊው የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያለው ሕንጻ ሹም ሊመደብ ይገባል፡፡ |
| በሕንፃ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ | 19.ሚ/ር መ/ቤቱ የሕንጻ ህጎች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች እና የስነ-ምግባር መርሆች መፈጸማቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙን ሊከታተልና ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 20.ሚ/ር መ/ቤቱ የግንባታ ውጤቶች የዲዛይን እድሜያቸውን ባገናዘበ ሁኔታ እድሳትና ጥገና የሚደረግበትን እና እንደአስፈላጊነቱ የሚወገድበትን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ከክልሎች ጋር በቅንጅት አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡ |

| | |
|---|---|
| | 21.ሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ሲል ተገንብተው ሥራ ላይ ያሉትን የዲዛይን ኮዶችና ስታንዳርዶች የደህንነት መስፈርት የማያሟሉ ሆነው ሲገኙ የማጠናከሪያ ዲዛይን እንዲዘጋጅላቸውና ግንባታቸውም እንዲተገበር የሚያደርግ የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 22.ሚ/ር መ/ቤቱ ግንባታቸው ከታለመላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ለመቀየር ሲፈለግ ለተጠየቀው የአገልግሎት ዘርፍ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት በመዘረጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 23.ሚ/ር መ/ቤቱ የሕንጻ ግንባታ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ (ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር) በየጊዜው የሚከለሱበት አሰራራ ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 24.ሚ/ር መ/ቤቱ የሕንጻ ግንባታ የሌሎችን አገሮችን ኮዶች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም ውጤታማ ተሞክሮ በመቀመር ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ስራ ላይ እንዲውል የልምድ ልውውጥ በማድረግ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 25.ከሕንጻ አዋጁ ጋር በተያያዘ ለሚ/ር መ/ቤቱ በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በተሰጡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 26.ሚ/ር መ/ቤቱ የሕንጻ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች አፈጻጸሙን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አሰራር መገንባቱን ዝርዝር ኢንስፔክሽን በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 27.ሚ/ር መ/ቤቱ በአዋጁና በህግ ማቀፎች ጥሰት በሚታይባቸው ከተሞችና ክልሎች አስተማሪ የሆነ የተጠያቂነት እርምጃ ለመውሰድ ከክልሎች ጋር በመሆን የተጠያቂነት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 28.ሚ/ር መ/ቤቱ ከማዕከል እስከ ከተማ አስተዳደር ባለው አደረጃጀት መረጃ የሚደራጅበትና ተደራሽ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ ባላድርሻ አካላት

| ተ.ቁ | የተቋም ስም | የከተሞች ስም | የሚገኙበት ክልል እና ከተማ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አማራ | ኦሮምያ | በደቡብ | አስተዳደር |
| 1 | የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን | አዲስ አበባ | | | | ✓ |
| 2 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ባለስልጣን | ድሬዳዋ | | | | ✓ |
| 4 | በፍኖተ ሰላም ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት | ፍኖተ ሰላም | ✓ | | | |
| 5 | በባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ህንጻ ሹም ጽ/ቤት | ባህር ዳር | ✓ | | | |
| 6 | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ | | ✓ | | | |
| 6 | የጭሮ ከተማ ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት | ጭሮ | | ✓ | | |
| 7 | በአዳማ ከተማ አስተዳደር የአዳማ ከተማ ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት | አዳማ | | ✓ | | |
| 8 | የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ጽ/ቤት | ቢሾፍቱ | | ✓ | | |
| | የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የኮንስትራክሽን ባለስልጣን | | | ✓ | | |
| 9 | የቡታጅራ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት | ቡታጅራ | | | ✓ | |
| 10 | በሀዋሳ ከተማ ኮንስትራክሽን መምሪያ | ሀዋሳ | | | ✓ | |
| 11 | በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ኮንስትራክሽን ቢሮ | | | | ✓ | |

## አባሪ 4፡ በሕንጻ ግንባታ ወቅት የደረሱ ሞትና የአካል ጉዳት

| ተ.ቁ | ጉዳት የደረሰበት ሰው | የግንባታው ዓይነት | የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ | የደረሰው ጉዳት | የጉዳቱ አይነት | ምንጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እሸቱ ሻንካሩ | 40/60 ኮንዶሚኒየም (ልዩ ስሙ ቦሌ በሻሌ ቃጢላ ኮንዶሚንየም) | በረከት እንዳሻው | ሞት | *በእቃ ማመላለሻ ሊፍት ውስጥ ዕቃ እየጫነ ከ6ተኛ ፎቅ ብሎኬት ወድቆበት ጭንቅላቱ በመመታቱ | ቀን_25/07/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/2085/2010 |
| 2 | አስችለኝ በልሁ | 40/60 ኮንዶሚኒየም ልዩ ስሙ ቦሌ ሃያት 49 ማዞርያ | - | ሞት | *ከስምንተኛ ፎቅ በመውደቁ | ቀን_03/10/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/371/2010 |
| 3 | አቡሽ እና አባተ ጎሹ | 22 ዳውን ታውን ቦሌ ክፍለ ከተማ | ሚክሲን ኢንጂነሪንግ እና ኢንጂነር አበበ አያሌው | ሞት | *ለፉቲንግ በተቆፈረ ጉድጓድ ላይ ሆነው እሰሩ እያለ የጎረቤት ሰርቪስ ቤት ተንዶ | ቀን_14/10/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/8413/2010 |
| 4 | አዝመራው በቀለ | 40/60 ኮንዶሚንየም ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ቦሌ አራብሳ | - | ሞት | *ሟች ከ13 ፎቅ ወደታች በዊንች ላይ ሆኖ እየወረደ ካቦ ተበጥሶ በመውደቁ | ቀን_26/07/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/3016/2010 |
| 5 | እያሱ ድካላ | 40/60 ኮንዶሚንየም ልዩ ቦታው 49 ማዞርያ | አፍሮጺዮን የሕንጻ ተቀቋራጭ | ሞት | *ከ14ኛ ፎቅ ላይ ሰራተኞች ብረት ወደ ዊንች እየጫኑ እያለ በማምለጡ መሬት ላይ የነበረውን ሰው ጭንቅላቱን በመመታቱ | ቀን_26/07/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/3015/2010 |
| 6 | ወርቁ መንግስቱ | 40/60 ኮንዶሚንየም | ሳይሲክ የሕንጻ ስራ ተቋራጭ | 1 ሰው ሞት 2 ሰው የአካል ጉዳት | *በዕቃ ማመላለሻ ሊፍት ተሳፍረው ብሎኬትና አምስት ጀሪካን ጭነው 3ኛ ፎቅ ሲደርሱ የሊፍት ካቦ ተበጥሶ ወደ መሬት በመውደቁ | ቀን_18/07/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/2020/2010 |
| 7 | ፍቃዱ አበራ | 40/60 ኮንዶሚኒየም ልዩ ስሙ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 49 ማዞርያ | በቀለ ሶርሳ የህንጻ ተቋራጭ | ሞት | ከኮንዶሚኒየም ፎቅ ላይ በመውደቁ | ቀን_26/07/2010 የደ.ቁ ግ/ፈ/ቁ/ባ/3006/2010 |
| 8 | 12 ሰው ላይ | በአራዳ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ 4 ኪሎ አካባቢ (እሪ በከንቱ ሰፈር) | የመንግስት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ባለቤትነትና በተክለ ብርሃን አምባዬ ተቋራጭ | ቀላል የአካል ጉዳት | 1. የባለሙያ ችግር/workmanship/<br>2. የአሰራር ስልት ክፍተት /methodology problem/<br>3. የኮንክሪት ፓምፕ/fresh concrete pressure/ አጠቃቀምን ክፍተት<br>4. የክትትል ችግር /supervision problem/<br>5. በ12 ሰው ላይ ቀላል የአካል ጉዳት | በቀን 13/02/2011 ከፌስ ቡክ የተወሰደ (የአዲስ አበባ ኮንስትራክሽን ቢሮ) |